22ኛ ዓመት ቁጥር 14
22nd Year No. 14

ባሕር ዳር ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም
Bahir Dar, October 30, 2017

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 51.06 ብር
Unit Price Birr 51.06

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 252/2009 ዓ.ም
የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ

Content

Proclamation No.252/2017
The Revised Rural Land Administration and Use Determination Proclamation of the Amhara National Regional State

አዋጅ ቁጥር 252/2009 ዓ.ም

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅን ለመወሰን የወጣ አዋጅ::

የኑሮ ደረጃውን ክልሉ ብሎም ሀገሪቱ ከደረሱበት ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገት ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ለማራመድ ይቻል ዘንድ አርሶ-አደሩም ሆነ ከፊል አርብቶ-አደሩ በያዘዉ የገጠር መሬት ላይ ያለውን የተጠቃሚነት መብት ይበልጥ ማስፋት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

Proclamation No. 252/2017

The Proclamation Issued to Determine the Revised Rural Land Administration and Use of the Amhara National Regional State.

WHEREAS, it is found necessary the farmers as well as semi-pastoralists better expand their right on using rural land so as to accommodate their living standard with the economical, social and political development where the region as well as the country has reached;

በክልሉ ውስጥ ተበታትኖ የሚኖረዉን አርሶ-አደርና ከፊል አርብቶ-አደር ወደ ተወሰኑ ማዕከላት በማሰባሰብ ሁለንተናዊ ለሆነ እድገት ተጠቃሚ የሚያደርጋቸዉን ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is needed to design a system that makes beneficial for all-rounded development _collecting the dispersed farmers and semi-pastoralists to some centers;

ይልቁንም የከፊል አርብቶ አደሩ ባህላዊ የመሬት አጠቃቀም እና አጠባበቅ ሥርዓት ጠቃሚና ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው እንደመሆኑ መጠን ሀገራችን ኢትዮጵያ የአርብቶ አደሮችን በመሬት የመጠቀም መብት አስመልክቶ በአህጉራዊና በዓለም-አቀፋዊ ደረጃ የፈረመቻቸውን ስምምነቶች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it is found necessary to apply in the region_the continental and international agreements that our country has already signed concerning the land using right of the semi-pastoralists since the semi-pastoralists' traditional land use and protection system is useful and has greater contribution;

የግል ባለሀብቱ እና አግባብ ያላቸዉ ድርጅቶች መሬትን በአግባቡ በማልማት፤ በመጠቀምና በመጠበቅ ረገድ የሚኖራቸዉን ተሳትፎ ለማጠናከር እና ጥረታቸዉ ከክልሉ መንግሥት የልማት ዓላማዎች ጋር አንዲቀናጅ ለማድረግ ያመች ዘንድ በፌደራሉ ሕገ-መንግሥት ለክልሎች በተሰጠዉ መሬትንና ተፈጥሮ ሀብቶችን የማስተዳደር ሥልጣን መሠረት ዝርዝር የገጠር መሬት አሥተዳደርና አጠቃቀም ሕግ ማዉጣትና በሥራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is needed to issue and apply particular rural land administration and use law based on the power given to regions to administer land and natural resources by the Federal Constitution so as to integrate the participation and effort of private investers' and pertinent organizations' concerning developing land appropriately, using and protecting with the regional government development goals;

በክልሉ ዉስጥ የገጠር መሬት ምዝገባ መረጃን በጥራት ለማደራጀትና ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ በአግባቡ ለማሰራጨት የሚያስችል ምቹ እና ደረጃዉን የጠበቀ የሕግ ማዕቀፍ በመፍጠር ሕጋዊ የመሬት ባለይዞታዎች የይዞታ ዋስትናቸዉ ተጠናክሮ በተፈጥሮ ኃብት ጥበቃ እና አጠቃቀም ረገድ ጉልህ ለውጥ እንዲያመጡ ማድረግ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is needed legal landholders bring a significant change, their holding right is being secured, in natural resource protection and use_ creating a favourable and standardized legal framework that can enable to organize a qualified rural land registration data and to disseminate it to the user society in the region;

ከዚሁ ጎን ለጎን ሕገ-ወጥ የወል መሬት ወረራን በመከላከልና በግልም ሆነ በወል ይዞታቸዉ ላይም ቢሆን ያልተፈቀዱ ግንባታዎችን በመቆጣጠር የገጠር መሬትን ዉጤታማና ዘላቂ አጠቃቀም ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it is found necessary to ensure effective and sustainable use of the rural land preventing illegal communal land invasion and controlling unpermitted buildings on private as well as communal holdings side by side;

ከመሬት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ግጭቶችን በመቀነስና የክልሉ መንግሥት እና ተጠቃሚዎች ራሳቸዉ አስተማማኝ የመረጃ አገልግሎት የሚያገኙበትን ዘመናዊ የመሬት መረጃ ስርዓት መዘርጋት እና ገቢራዊ ማድረግ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is needed to designe and implement a modern information system which the regional government and users themselves get reliable information service_ reducing conflicts arising from land-related cases;

በተለያዩ የክልሉ የስነ-ምህዳር ቀጠናዎች ላይ ተመስርቶ ፈርጀ-ብዙ የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ በማውጣትና በመተግበር የተፈጥሮ ሀብቶችን በዘላቂነት በመጠበቅና በማልማት ለመጪዉ ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል አስተዳደሩንና አጠቃቀሙን በሕግ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, it is necessary to proclaim the administration and use in law _ issuing and implementing multi-dimensional rural land use plan on the basis of different ecological zones of the region so as to transfer to the next generation protecting and developing natural resources sustainably;

ሴቶች፣ ሕጻናት፣ አካል-ጉዳተኞች፣ አቅመ-ደካሞች እና አረጋዊያን ያላቸዉ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት እንዲጠናከር ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚደነግግ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is needed to design a system that proclaims particular situations in order to strengthen the using rights of women, children, disables, weaklings and ageds on the rural land;

በክልሉ ዉስጥ አንዳንድ የገጠር ቀበሌዎች ወደ አቅራቢያዉ የከተማ አሥተዳደር ክልል በሚጠቃለሉበት ወይም የገጠር መሬት ለሕዝብ አገልግሎት እንዲዉል በሚፈለግበት ጊዜ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ከይዞታቸዉ እንዲነሱ ሲደረግ ተገቢና ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ የሚያገኙበትንና በዘላቂነት የሚቋቋሙበትን አሠራር በሕግ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it is found necessary to proclaim a procedure by law that enables landholders and users to get the commensurate compensation in advance and to re-settle sustainably when the rural landholders' and users' land is expropriated embraced under a city administration and when their land is needed for public service in some areas of the region;

እነዚህንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች አስመልክቶ በሥራ ላይ ያለዉ ሕግ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሕግጋትና ደንቦች ተፈፃሚነት በማረጋገጡ ረገድ ውስንነት ስለሚታይበት ክልሉ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ ጋር ይበልጥ ተጣጥሞ መሻሻል እንደሚገባዉ በመታመኑ፤

WHEREAS, it is believed that the existing law has limitation to ensure the implementation of other appropriate laws and regulations concerning these and similar issues, and it should be amended_being in line with the development level of the region;

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 /1/ እና በፌዴራሉ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 ዓ.ም አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, the Amhara National Regional Council pursuant to the powers vested in it under Article 49 sub-article 3/1/ of The Revised Regional Constitution and The Federal Democratic Republic of Ethiopia Rural Land Administration and Use Proclamation No 456/2005, Artcicle 17 sub-article 1 of the Federal Government, here issued this proclamation.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1. አጭር ርዕስ

1. Short Title

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 252 /2009 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

This proclamation may be cited as “The Revised Rural Land Administration and Use Determination Proclamation No. 252/2017 of the Amhara National Regional State.”

2. ትርጓሜ

2. Definitions

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

In this proclamation, unless the context require otherwise:

1. ""የገጠር መሬት" ማለት በገጠር የአስተዳደር ወሰን የተጠቃለሉ የገጠር መሬት ይዞታዎችን እና በከተሞች የአስተዳደርና የፕላን ወሰን ክልል ውስጥ ያለ ማንኛውም የገጠር መሬት ነው፡፡

1. “**Rural Land**” means a rural landholding found with in the limit of a rural land administration and any other rural land in cities’ administration and a plan boundary.

2. **"የገጠር መሬት አስተዳደር"** ማለት የገጠር መሬት ይዞታ መብት የሚሰጥበት፣ ዋስትና የሚረጋገጥበት፣ የመሬት ኃብት የኪራይና የሊዝ ዋጋ የሚተመንበት፣ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚተገበርበት፤ በመሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ ግጭቶች የሚፈቱበትና ግዴታዎች የሚተገበሩበት እንዲሁም ከላይ የተመለከቱትን ጉዳዮች አስመልክቶ መረጃ እየተሰበሰበ የሚተነተንበትና ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭበት ሂደት ነው።

2. "**Rural Land Administration**" means the process whereby rural landholding right is provided, guarantee is secured, the rent and lease value of land is estimated, the land use plan is implemented, disputes arising between land users are resolved and obligations are enforced as well as data is distributed to users being collected and analyzed concerning the above indicated issues.

3. **"የመሬት አጠቃቀም"** ማለት የገጠር መሬትን በእንክብካቤ ይዞ ዘላቂነት ባለው መንገድ ለተሻለ ጠቀሜታ እንዲውል የሚደረግበት ሂደት ነው።

3. "**Land Use**" means the process where by rural land is conserved and sustainably used in a manner that gives better out put.

4. **"የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ"** ማለት አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የገጠር መሬት ሊሰጥ ከሚችለው የተለያዩ የመሬት አጠቃቀም አማራጮች መካከል የመሬት መሳሳቆልንና የአካባቢን ብክለት ሳያስከትሉ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙት አማራጮች ተወዳድረው የሚወሰኑበትና ተግባራዊ የሚደረጉበት የአሠራር ዘዴ ነው።

4. "**Land Use Plan**" means a practice whereby the options that give greater economic benefits without cuasing land degradation and environmental pollution are determined and implemented from among the different use options_a rural land can give on the basis of physical, economical and social information.

5. **"አርሶ-አደር"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት መደበኛ ወይም ቋሚ መተዳደሪያው የግብርና ሥራ የሆነ ማናቸውም ሰው ሲሆን ከፊል አርብቶ-አደሮችንም ይጨምራል።

5. "**Farmer**" means any person, whose regular or permanent livelihood is agricultural work, based on this proclamation, including semi-pastoralists.

6. **" ልጅ"** ማለት በሥጋ የተወለደ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ነው፡፡

6. "**Child**" means a biological or adopted child.

7. **"ተጧሪ"** ማለት በእድሜ መግፋት፣ በበሽታ፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ምክንያቶች ሳቢያ በራሱ አቅም ገቢ የሚያስገኝ ሥራ መሥራት የተሳነውና ለመተዳደሪያው የሌሎችን ሰዎች እርዳታ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

7. "**Maintenance creditor**" means any person who is unable to work independently in his potential for his livelihood due to aging, illness, physical injury or other related cases, and seeks the assistance of other persons.

8. **"ጧሪ" ወይም "ተንከባካቢ"** ማለት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 7 ሥር የተመለከተውን ወገን በሥሩ አድርጉ ወይም በቅርበት ሆኖ መሠረታዊ አገልግሎቶችን እየሰጠ የሚደግፍ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

8. "**Maintenance debtor**" or "**support provider**" means any person who supports the party mentioned under sub-article 7 of this article by giving basic needs letting with him or close to him.

9. **"የቤተ-ሰብ አባል"** ማለት ከመሬት ባለይዞታው ጋር በቋሚነት አብሮ የሚኖርና የራሱ የሆነ ቋሚ መተዳደሪያ የሌለው የይዞታ ባለመብቱን አርሶ-አደር ገቢ በመጋራት የሚተዳደር ማንኛውም ሰው ነው፡፡

9. "**Family Member**" means any person that has no his own permanent livelihood instead who shares the revenue of the farmer, lives permanently with the landholder.

10. **"አቅመ-ደካሞች"** የሚለው ሀረግ በእድሜ ከመግፋት፤በበሽታ ከመጠቃት ወይም በምጣኔ-ሀብት ረገድ ከመደህየት የተነሳ በሁለንተናዊ አቋማቸው ተዳክመው የሚታዩ ዜጎችን የሚገልጽ ነው፡፡

10. "**Weaklings"** This phrase describes all-rounded weaken physical appearances of citizens due to aging, illness or econonmical poorness.

11. **"የመሬት ምዝገባ"** ማለት በገጠሩ አካባቢ በመሬት የመጠቀም መብትና ባለይዞታነት የሚገለጽበት የመረጃ ማሰባሰብና የማጠናቀር ሂደት ነው፡፡

11. "**Land Registration**" means a process of information collection and organization of rural land use right and landholdingness is manifested in the rural areas.

12. **"የገጠር መሬት መረጃ ስርዓት"** ማለት የገጠር መሬት ነክ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በመተንተንና በአግባቡ እንዲያዙ በማድረግ ለተለያዩ ተጠቃሚ ክፍሎች የማሰራጨት ሥርዓት ነው፡፡

12 "**Rural Land Data System**" means a system in which land-related data are being collected, organized, analyzed, and properly kept to be distributed for different beneficiary parties.

13. **"ማሳ"** ማለት በአንድ ቦታ ላይ የሚገኝ በድንበር የተከለለና በባለይዞታው ስር ያለ የመሬት ክፍል ነው።

13. "**Plot**" means a part of plot under a landholder found in a place and defined by a boundary.

14. **"አነስተኛ የማሳ መጠን"** ማለት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ መሠረት በይዞታነት የሚሰጥ ዝቅተኛ የማሣ "ልክ" ነው።

14. "Minimum Plot Size" means the least plot of land to be given to as holding in accordance with a regulation to be issued to implement this proclamation.

15. **"*መሠረታዊ ካርታ*"** ማለት የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን የያዘና ለተወሰነ ዓላማ የሚያገለግሉ ካርታዎችን ለመስራት በመነሻነት የሚያገለግል ካርታ ሲሆን በብሔራዊው የካርታ ሥራ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ላይ ተመሥርቶ የሚዘጋጅና ከብሔራዊ የኮርድኔት ሥርዓት ጋር የተገናኘና ጥቅል ዓላማ ያለው ካርታ ነው።

15. "**Fundamental Map**" means a map containing primary level data used for preparing maps for specific objectives which is prepared based on the national map making control points, and has a general objective_connected with the national coordinate system.

16. **"የማሳ ካርታ"** ማለት ማንኛውም ገጠር መሬት ባለይዞታ በአንድ ማሳ ላይ ያለው መብት በውል ተረጋግጦ በይዞታው ስር የሚገኘው ይኸው ማሳ የት እንደሚገኝ፣ የማሳውን ቅርፅ፣ ጠቅላላ ስፋቱንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች የሚያሳይ ካርታ ነው።

16. "**Map of a Plot**" means a map that shows the location, shape, total area and other related data found in a given plot being secured the right of a landholder in a contract.

17. **"የቀበሌ ካዳስተር ካርታ"** ማለት ለካዳስተር ቅየሳ ሲባል በዚህ አዋጅ ውስጥ የተጠቀሱትን መሠረታዊ የካዳስተር መረጃዎች የያዘ ሆኖ በክልሉ አማካኝነት ለየትኛውም የገጠር ቀበሌ የሚዘጋጅና ለቅየሳ ሥራ መነሻ በመሆን የሚያገለግል ካርታ ነው።

17. "**Cadaster Map of a Kebele**" means a map containing the basic cadaster data for the cadaster surveying, mentioned in this proclamation, which is prepared by the region for every kebele used to be a benchmark for a surveying work.

18. **"ካዳስተር"** ማለት አንድን ማሳ መነሻ አድርጎ በመሬት ላይ በወቅቱ የሚገኙትን መብቶችን የሚያመላክቱ ሰነዶችንና ሌሎች መረጃዎችን የያዘ መረጃ ስርዓት ነው፡፡

18. "**Cadaster**" means a land data system that contains the documents and data indicating current rights on the land in line with a given plot.

19. **"የካዳስተር ቅየሳ"** ማለት የአንድን የገጠር መሬት ባለይዞታ ማሳ ስፋትና የሚገኝበትን አካባቢ ለመወሰን እንዲረዳ የድንበር ምልክቶችን፣ አመላካች ነጥቦች እና ማዕዘኖችን በመስክ ቅየሳና በርቀት ምስሎች ተደግፎ የመለካት ወይም የድንበር ለውጥ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚደረገውን የቅየሳ ሥራ ወይም የሚከፈሉ መሬቶችን በመለየት፣ ይዞታን በማሳወች ከፋፍሎ በወረቀት የመንደፍና የመቀየስ ተግባር ነው፡፡

19. "**Survey of a Cadaster**" means the function of measuring demarcations, reference points and corners in field surveying and distance pictures or identifying, drafting and surveying landholding on the rural land farm in a paper when there is a change of boundary so as to enable to determine the area and the location of a plot of the landholder.

20. **"የቀበሌ ነዋሪ"** ማለት መደበኛ መቀመጫውን በአንድ ቀበሌ አድርጎ መሠረታዊ አገልግሎቶችንና ማኅበራዊ ጥቅሞቹን በዚያው ቀበሌ ውስጥ የሚያገኝ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

20. "**Kebele Resident**" means any person who regularly resides in a certain kebele getting the basic services and social benefits in it.

21. **"የግል ይዞታ"** ማለት ከወልና ከመንግሥት ይዞታ ውጪ ሆኖ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ባለይዞታዎች የጋራ ይዞታ ስር ያለ የገጠር መሬት ነው፡፡

21. "**Private Holding**" means land under the possession of one person or more than one person excluding the government or communal holdings.

22. **"የወል ይዞታ"** ማለት አርሶ-አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ-አደሮች በጋርዮሽ ይዘው ሳይከፋፈል በአንድነት ለግጦሽ፣ ለደንና ለማኅበራዊ አገልግሎቶች የሚጠቀሙበት የገጠር መሬት ነው፡፡

22. "**Communal Holding**" means the rural land that farmers or semi-pastoralists use for grazing, forest and social services holding as a communal holding not being divided.

23. **"የመንግሥት ይዞታ"** ማለት በክልሉ ውስጥ በግል ወይም በወል ያልተያዘ የገጠር መሬት ሲሆን የመንግሥት ተቋማት ይዞታዎችን፣ የደን መሬቶችን፣ የዱር እንስሳት መጠለያዎችንና ጥብቅ ስፍራዎችን፣ የማዕድን ማውጫ ቦታዎችን፣ ፓርኮችንና በወንዞችም ሆነ በበሀይቆች አካባቢ የሚገኙ ስፍራዎችን ያጠቃልላል፡፡

23. "**Government Holding"** means the land not being held either privately or communally in the region; it includes holdings of government institutions, lands of forest, sanctuaries and protected places, mining places, parks and places found around rivers as well as lakes.

24. **"የይዞታ መብት"** ማለት ማንኛውም አርሶ-አደር፣ ከፊል አርብቶ-አደር ወይም በሕጉ መብት የተሰጠው ማናቸውም ሌላ አካል በዚህ አዋጅ መሰረት የተረጋገጡለትን የገጠር መሬት ባለይዞታ የመሆን፣ በመሬቱ ላይ ንብረት የማፍራት፣ ያፈራውን ንብረት የማስተላለፍ፣ ከመሬቱ ያለመፈናቀል፣ መሬቱን ለግብርናና ለተፈጥሮ ሃብት ልማትም ሆነ ለሌሎች ሕጋዊ ተግባራት የማዋል፣ በራሱ የመጠቀም፣ የማከራየት፣ የማውረስ፤ በስጦታ የማስተላለፍና የመሳሰሉትን መብቶችን የሚያጠቃልል ነው፡፡

24. "**Holding Right**" means the rights of any farmer, semi-pastoralist or any other person vested with rights on it in accordance with this proclamation to be the holder of land, to create assets on the land, to transfer an asset he created, not to be displaced from his holding, to use his land for agricultural and natural resource development and other activities, to rent his land, to transfer it in the form of donation, succession and includes the like.

25. **"የመሬት ባለይዞታ"** ማለት በአንድ የገጠር መሬት ላይ የይዞታ መብት ያለው ግለ-ሰብ፣ ቡድን ወይም ማህበረ-ሰብ፣ የመንግሥት አካል፣ ማኅበራዊ ተቋም ወይም ሌላ የሕግ ሰውነት ያለው አካልነው።

25. "**Landholder**" means any individual, group or community, government, social institutions or other legal body having the right of holding on a given rural land.

26. **"የመሬት ተጠቃሚ"** ማለት የገጠር መሬትን የመገልገልና በምርቱ የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው።

26. "**Land User**" means any person vested with rights to use rural land and its fruits.

27. **"አነስተኛ ይዞታ"** ማለት ምርት በመስጠት አቅሙ የአንድን አርሶ-አደር፤ ወይም ከፊል አርብቶ-አደር የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ ለእንስሳት ግጦሽ፣ ለቤት መሥሪያና ለጓሮ አትክልት ልማት በቂ ነው ተብሎ ስልጣን ባለው አካል አማካኝነት በይዞታነት የሚሰጥ ዝቅተኛ የመሬት መጠን ነው።

27. "**Minimum Holding**" means the minimum piece of land given by an authorized body to a farmer or semi-pastoralist which is decided to be enough for a farmer in its productivity to ensure food security, grazing, building a house and for growing vegetables.

28. **"ሌላ ንብረት"** ማለት ከመሬት በስተቀር በመሬቱ ላይ የተፈራና የማይንቀሳቀስ ማንኛዉም ንብረት ነዉ።

28. "**Other property**" means any immovable property produced on the land except the land itself.

29. **"ኪራይ"** ማለት ማንኛውም አርሶ-አደር በዚህ አዋጅ መሠረት ያገኘውን የገጠር መሬት ይዞታ ወይም የመጠቀም መብት ለተወሰነ የጊዜ ገደብ ለሌላ ሰው በውል ሰጥቶ የአይነት ወይም የገንዘብ ጥቅም እየተቀበለ አገልግሎት ላይ እንዲውል የሚያደርግበት ስራት ነው።

29. "**Rent**" means a system in which any farmer cuases the use of his rural landholding or right of use to be transferred to another person through contract for a limited period of time receiving either in kind or in cash benefit.

30. **"ሊዝ"** ማለት ማንኛውም የግል ባለሃብት የገጠር መሬት ይዞታን ለተወሰነ ጊዜና በሕግ ለተፈቀደ አገልግሎት ከክልሉ መንግሥት የሚወስድበት አሠራር ሲሆን የሊዝ ዘመኑ ፀንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ በመሬት የመጠቀም መብቱን ለአበዳሪ ተቋማት የዕዳ ዋስትና አድርጎ እስከ ማስያዝ የሚደርስበት አሰራር ነው።

30. "**Lease**" means the operation in which any private investor takes rural land for a limited time to legally permitted service from the regional government including the rights of mortgage for creditor institutions untill the effective date of the contract to use the land.

31. **"ብሎኪንግ"** ማለት የኢንቨስትመንት መሬትን ወጥ በሆነና ስርዓት ባለው መንገድ በብሎክ የመከፋፈል ዘዴ ነው።

31. "**Blocking**" means a consistent and systematic method of dividing investment land in blocks.

32. **"የመስኖ መሬት ሽግሽግ"** ማለት ዘመናዊ የመስኖ ግንባታ በተካሄደባቸዉ የገጠሩ አካባቢዎች ለመስኖ መሰረተ-ልማት አውታሮች ግንባታ ሲባል መሬት የተወሰደባቸዉን ባለይዞታዎች ከተጠቃሚዎች በኩል ለማተካካት እንዲቻል፤የተበታተነዉን ይዞታ ለመንከባከብ በሚያመች ሁኔታ እስከተቻለ ድረስ በአንድ አካባቢ ለማሰባሰብና የመስኖ ዉሃ ለማጠጣት ምቹ በሆነ ቅርፅ የሚካሄድ ክፍፍል ነዉ።

32 "**Irrigation Land Re-distribution**" means a type of division to set off displaceds _for the sake of irrigation chord from landholders, to make the dispersed land in one area as much as possible and to make suitable for watering the irrigation where in areas of modern irrigation Construction is taken place.

33. **"ድልድል"** ማለት በአንድ የገጠር ቀበሌ ዉስጥ ነጻ ነው ተብሎ የተመዘገበና የተያዘ መሬት በነዋሪው ህዝብ ውሳኔና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት መሬት ለሌላቸው ወይም ላነሳቸው ሰዎች የመስጠት ተግባር ነው፡፡

33. "**Distribution**" means the operation that a plot of land is given for landless or those who have little plot of land from a given rural kebele where free land is registered in accordance with decision of the resident population and provisions of this proclamation.

34. **"የሕዝብ አገልግሎት"** ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ሆነው እንደ መንግሥት መሥሪያ ቤት፣ ትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋም፣ የገበያ ስፍራ፣ የመንገድ መሰረተ-ልማት፣ የወታደር ካምፕና እነዚህን የመሳሰሉትና በክልሉም ሆነ በፌደራሉ መንግሥታት አማካኝነት ለሕዝብ እድገት ይጠቅማሉ ተብለው በገጠር መሬት ላይ የሚከናወኑ ተግባራትን ያጠቃልላል፡፡

34. "**Public Service**" means a service given to the public either directly or indirectly such as government office, school, health institution, market place, road infrastructure, military camp, and soforth functions decided by the Regional and the Federal Governments deemed to be useful to the public.

35. **"የአስተዳደር ወሰን"** ማለት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ዞኖች፣ወረዳዎችና ቀበሌዎች አንዱ ከሌላው ጋር የሚዋሰኑበት ድንበር ሲሆን ከተሞች ከየገጠሩ አስተዳደሮች ጋር የሚገናኙባቸውን ስፍራዎች ይጨምራል፡፡

35. "**Administrative Demarcation**" means the adjoint boundaries where zones, weredas and kebles in the region are demarked each other; it includes boundaries of towns from rural administrations.

36. **"በከተማ አስተዳደር የተጠቃለለ የገጠር ቀበሌ"** ማለት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የከተማነት ደረጃ በሰጠው በየትኛውም ከተማ ወሰን የተካለለ ወይም የታቀፈ የገጠር ቀበሌ ነው፡፡

36. "**Rural Kebele Embraced under a City**" means a rural kebele demarcated or embraced under any city that the council of regional government has given the level of urbaness.

37. **"በከተማ አስተዳደር የተጠቃለለ የገጠር ቀበሌ ነዋሪ"** ማለት መደበኛ መኖሪያውን በከተማ አስተዳደር ወሰን በሚገኝ የገጠር ቀበሌ ውስጥ ያደረገና መሰረታዊ አገልግሎቶቹንም ሆነ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞቹን በዚያው እያገኘ በራሱ ስም የገጠር መሬት ይዞታ መብት ያለውም ይሁን የሌለው ማንኛውም ሰው ነው፡

37. "**A Rural Kebele Resident Embraced under a City"** means any person, whether he has a rural landholding or not, who made his regular living in a rural keble found under a city administration and gets his fundamental services as well as social and economical benfits thereby.

38. **"የገጠር ቀበሌ ማዕከል"** ማለት በጥናት ተደግፎ በነዋሪው ህዝብ አስተያየት አግባብ ባለው የወረዳ አስተዳደር በኩል ለመኖሪያነትም ሆነ ለሌሎች የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አገልግሎቶች የተመረጠ ማዕከል ነው፡፡

39. **"ሕገ-ወጥ ይዞታ"** ማለት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የተያዘና አግባብ ባለው አካል እውቅና ያልተሰጠው ማናቸውም የገጠር መሬት ይዞታ ነው፡፡

40. **"ሕገ-ወጥ ግንባታ"** ማለት ሕገ-ወጥ በሆነ ይዞታ ወይም በሕጋዊ ይዞታ ላይም ቢሆን በዚህ አዋጅ ከተፈቀደዉ ዉጭ የተከናወነ ማናቸውም አይነት ግንባታ ነው፡፡

41. **"ካሳ"** ማለት በሕጋዊ መንገድ ተይዞ የነበረን የገጠር መሬት ይዞታ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል እንዲለቅ ሥልጣን ባለው አካል የሚወሰንበት ማንኛውም ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ ከመሬቱ በሚፈናቀልበት ወቅት ከቦታው በሚያነሳው ንብረት ወይም በመሬቱ ላይ ባደረገው ማናቸውም ዓይነት ማሻሻያ ምትክ በገንዘብም ሆነ በዓይነት፣ ወይም በሁለቱም በቅድሚያ የሚፈፀም ተመጣጣኝ ክፍያ ነው፡፡

42. **"መልሶ ማቋቋም"** ማለት በሕግ መሠረት ካሳ ተከፍሏቸዉ የመሬት ይዞታቸዉ ለሕዝብ አገልግሎት ሲባል ከመወሰዱ የተነሳ የተፈናቀሉ ባለይዞታዎች ቀደም ሲል የነበራቸዉን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማስቀጠል ወይም ለማሻሻል በክልሉ መንግስት የሚከናወን ተግባር ነዉ፡፡

38. "**Center of Rural Kebele**" means a center preferred by the resident population supported by a research being used as a center of rural kebele and approved by the pertinent wereda administration for living as well as other different economical, social and political services.

39. "**Illegal Holding**" means any rural landholding held in illegal means and not given recognition by a pertinent body.

40. "**Illegal Construction**" means any kind of construction made on an illegal holding or out of permision in this proclamation even if it is on the legal holding.

41. "**Compensation**" means a commensurate payment made in advance either in cash or in kind or in both forms to any legal landholding or user, when decided to leave by an authorized body for the sake of public purpose, for a replacement of property he displaces or any improvement he made on the land.

42. "Re-settlement" means a work done to maintain or improve the social and economical benefits they had before of those legally expropriated and displaced landholders, being payed compensation _by the regional government, for the sake of public service.

43. **"ቋሚ መተዳደሪያ"** ማለት ከግብርና ውጪ ሆኖ ግብር እየተከፈለበት የሚከናወንና ገቢ ሊያስገኝ የሚችል ሌላ ማናቸውም አይነት ቋሚ ሥራ ነዉ።

43 "**Permanent Livelihood**" means any other permanent work which is a source of income and taxable_ being other than agricultural work.

44. **"አስተዳደራዊ ዉሳኔ"** ማለት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ባለጉዳዮች፣ በይዞታ መብትና መጠቀም ጥያቄ ሲያቀርቡ ወይም በተቃራኒው ግዴታወቻቸውን ሳይወጡ ሲቀሩ አግባብነት ያላቸዉን የመረጃ ምንጮች በመጠቀምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በሕዝብ በማስተቸት ጉዳዩ በሚመለከተው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካል ከተጣራ በኃላ በጽሁፍ የሚሰጥ ማናቸውም ውሳኔ ሲሆን ከገጠር መሬት ልኬታ፤ ምዝገባ፤ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አሰጣጥ፣ ከመሬት አጠቃቀም እቅድ፣ ከይዞታ መታጣትና ከሌሎች ተዛማጅ እርምጃዎች ጋር በተገናኘ የሚተላለፉ ትዛዞችን ያጠቃልላል።

44. "**Administrative Decision**" means a written decision given by the rural land administration and use in relation with measurement of rural land, registration, giving land certificate, land use plan, losing of holding right including passed orders related to other measures_by using pertinent information sources and making to be criticized and insured by the public when it is necessary, causing to be checked by the pertinent land administration and use body, when one or more than that applicant presents a request on the holding right or to the contrary when they do not carry out their responsibilities.

45. **"መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት"** ማለት በትርፍ ላይ ያልተመሰረተ ተግባር ለማከናወን የተቋቋመና በራሱ ገቢ የሚተዳደር ማናቸውም ድርጅት ነዉ።

45. "**Non-governmental Organization**" means any organization established to carry out a non-profit activity and administered by its income.

46. **"ቢሮ"** ማለት የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ነው።

46. "**Bureau**" means the Regional Rural Land Administration and Use Bureau.

47. **"ሰው"** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

47. "**Person**" means any natural person or legal person.

3. የጾታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

4. የአዋጁ ተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ በክልሉ ውስጥ በሚገኝ የትኛውም የገጠር መሬት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ለደን፣ ለዱር እንስሳት ጥበቃ፣ ለብዝኃ-ሕይወት ሀብት፣ ለተፈጥሮ ሀብትና ለአካባቢ ጥበቃም ሆነ ለማዕድን ልማትና ለመሳሰሉት ተግባራት የተከለሉ መሬቶችን ማልማትና መንከባከብን በተመለከተ የወጡ ልዩ ሕጎች እንደየተደነገጉባቸው መስኮች ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

ክፍል ሁለት

የገጠር መሬት ስለማግኘት፣ ስለመጠቀም እና ስለማስተዳደር

5. መሠረታዊ መርሆዎች

1. በክልሉ ውስጥ የገጠር መሬት ባለቤትነት መብት የክልሉ መንግሥትና የሕዝብ ነው፡፡ በመሆኑም የመሬት ይዞታን በሽያጭም ሆነ በሌላ ንብረት በመለወጥ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም፡፡

3. Gender Reference

The expression in this proclamation in masculine gender also includes the feminine.

4. Scope of Application

1. This proclamation shall be applicable on any rural land found in the Region.
2. Notwithstanding the provision stated undert sub-article 1 of this Article, special laws will continue on application as the fields they have been stipulated concerning the delineated lands for forestery, wildlife protection, biodiversity resource and environmental protection, as well as mine development and the like.

PART TWO

ACQUIRING RURAL LAND, USING AND ADMINISTERING

5. Fundamental Principles

1. The right to ownership of land is vested in the state and the public. As a result, it is impossible to transfer the land holding to a third party either in sale or in exchange by other property.

2. በክልሉ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም አርሶ-አደር በፆታም ሆነ በሌላ በማናቸውም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግበት የገጠር መሬት ይዞታ በነጻ የማግኘት እኩል መብት አለው።
3. በክልሉ ውስጥ አርሶ-አደሮች ያላቸው የገጠር መሬት ይዞታ መብት የጊዜ ገደብ የለውም።
4. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት በሕዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

5. የመሬት አጠቃቀም በእቅድና አካባቢን በመንከባከብ ላይ አተኩሮ የሚፈጸም ይሆናል።

6. የገጠር መሬት ድልድል በሚካሄድበት ጊዜ ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአቅመ ደካሞች፣ ለሴቶችና ለአረጋውያን ቅድሚያ እንዲሰጥ የሚያደርግ የአሠራር ስርዓት ተቀርጾ በሥራ ላይ ይውላል፣
7. በገጠር ኢንቨስትመንትን የማስፋፋት ተግባር ለወጣቶች የሥራ እድል ፈጠራና የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማፋጠን ላይ አልሞ የሚፈጸም ይሆናል።

6. የይዞታ ዓይነቶች

በገጠር መሬት ላይ ያሉ እና በዚህ አዋጅ ጥበቃ የተደረገላቸው የመሬት ይዞታ አይነቶች የግል፣ የወል እና የመንግሥት ናቸው።

7. የገጠር መሬት ባለይዞታ ስለመሆን

1. የገጠር መሬት ባለይዞታ መሆን የሚችለው የክልሉ ነዋሪ የሆነና በዋነኛነት በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም በዚሁ የሙያ መስክ ለመተዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ነው።

2. Any farmer living in the region has equal right to aquire the rural land holding free of charge without any discrimination of sex or any other reason.

3. The holding right of rural land in the region shall not have time limit.

4. The system of rural land administration and use shall be based on public participation.

5. The land use shall be implemented focusing on a plan and protecting environment.

6. When a rural land is being distributed, a system that makes to give priority for children who have lost their parents, disables, weaklings, women and ageds will be designed and implemented.

7. The investment expanasion work in rurals shall be implemented gearing towards job creation for the youths and fostering technology transfer.

6. Types of Holding

The types of holding that are found on the rural land and protected in this proclamation are private, communal and government holdings.

7. Being a Rural Landholder

1. Any person who resides in the region and mainly engaged in agricultural activities or who wants to engage in the same activity can be the rural landholder.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተደነገገዉ ቢኖርም ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ ደንብ የሚደነገግ ሆኖ የሚከተሉት ወገኖች በዚህ አዋጅ መሠረት የገጠር መሬት ባለይዞታ ከመሆን አይታገዱም፡-

ሀ. በተለያዩ ጊዜያት በብሔራዊም ሆነ በክልላዊ ምርጫዎች ተወዳድረው በማሸነፍ በሕዝብ ተወካዮችም ሆነ በክልል ምክር ቤቶች በቋሚነት ያገለግሉ ዘንድ አካባቢያቸውን ለጊዜው እንዲለቁ የተገደዱ አርሶ አደሮች ወይም ከፊል አርብቶ አደሮች፣

ለ. አነስተኛ የወር ገቢ በሚያስገኙና እንደ ዘብ፣ ጥበቃ፣ ጽዳት፣ ተላላኪና ፖስተኛ ባሉ የሥራ ደረጃዎች ላይ ተቀጥረው የሚያገለግሉና በክልሉ ሲቭል ሰርቪስ የሥራ መደብ ዝቅተኛ ለተባለው መደብ የተወሰነው ደመወዝ የሚያገኙ የግል፣ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሠራተኞች፣

ሐ. በጡረታ ገቢ የሚተዳደር ማንኛውም ሰው፡፡

8. ስለይዞታ መብት አፈጻጸም

1. ለአርሶ-አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በዚህ አዋጅ መሠረት በተሰጣቸው የገጠር መሬት ይዞታ ላይ ሙሉ የባለይዞታነትና የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

2. Notwithstanding the provision under sub-article /1/ of this Article, the details to be provided by a regulation in the future, the following parties, in accordance with this proclamation, are not prohibited from being the rural landholder:

A. Farmers or semi-pastoralists that are forced to leave temporarly their locality, winning in different times in national or regional elections, to serve in the House of Peoples Representatives as well as in the regional councils permanently.

B. Private, government and non-governmental organization employees hired in the least monthly income levels such as sentry, guard, janitor, runner and postperson, and those who get the decided salary working at the least position to be said by the region's civil service.

C. Any person who lives on pension.

8. Implementation of Holding Right

1. Farmers and semi-pastoralists have a full holding and using right on their rural land given by this proclamation.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ስር የተመለከተውና (የይዞታ መብት) የሚለው ሐረግ በእጅ ያለን የገጠር መሬት ለሶስተኛ ወገኖች በውርስ ወይም በስጦታ የማስተላለፍ፣ በሌላ መሬት የመለወጥ፣ እንዲሁም በመሬቱ የመጠቀምም ሆነ በመሬቱ ላይ ያለማዉን ማናቸውንም ዓይነት ሀብት ወይንም ሁለቱንም ቢሆን የማከራየት ወይም ለአበዳሪ ድርጅቶች ዋስትና አድርጎ በእዳ የማስያዝ መብቶችን ያጠቃልላል።

9. ስለይዞታና የመጠቀም መብቶች መከበር

1. የማንኛውም ሰው የገጠር መሬት ይዞታ በሕግ የተጠበቀ ነው። ስለሆነም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 እና 26 ስር በተደነገገው መሰረት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው የያዘውን መሬት ከፈቃዱ ውጪ እንዲለቅ አይገደድም፣

2. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ከተደነገገው ውጭ በሆነ ምክንያት ይህንኑ የመጠቀም መብቱን አያጣም።

10. የገጠር መሬት ስለማግኘት

1. ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ በክልሉ ውስጥ የሚኖርና በግብርና ሥራ ለመተዳደር የመረጠ ማንኛውም ሰዉ በዚህ አዋጅ መሠረት የገጠር መሬት በነፃ የማግኘት መብት አለው። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

2. The phrase indicated and (holding right) under the provision of sub-article (1) of this Article, includes rights of transfering of land in hand to third parties via succession or donation, exchanging by other rural land as well as renting, mortgaging to lending organizations, being served by a land or any kind of wealth produced on land or both.

9. Respect of Holding and Use Rights

1. Any person's rural landholding is protected by law. Hence, any person is not obliged to leave his land without his consent unless it is for using the land to public service as provided in Articles 21 and 26 in this proclamation.

2. Any person given the right to use rural land may not lose this using right by any reason except the provisions by this proclamation or a regulation to be issued to implemt this proclamation.

10. Acquiring Rural Land

1. Any person being 18 and above years old residing in the region and who preferred to engage in argricultural activity has the right to aquire rural land free of charge in accordance to this proclamation. Details will be determined by a regulation.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተደነገገው ቢኖርም 18 ዓመት ያልሞላቸው እና ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ሕፃናት በሕጋዊ አሳዳጊዎቻቸው ወይም በሞግዚቶቻቸው አማካኝነት የሚተዳደሩበት መሬት የማግኘት መብት አላቸው።

2. Notwithstanding the provision under sub-article /1/ of this Article, children who have lost their parents under 18 years old have the right to aquire land to support their livelihood through their legal guardians.

3. ባለትዳር የሆነ ማንኛውም ሰው የግልም ሆነ ከተጋቢው ጋር የሚጋራው የመሬት ይዞታ የሌለው ከሆነ እንደ ማንኛውም መሬት-አልባ አመልካች የገጠር መሬት እንዲሰጠው የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው። የሚያገኘው መሬትም የግል ይዞታው ሆኖ ይመዘገብለታል።

3. Any married person has the right to request and aquire as any landless if he has no private as well as a landholding he shares with his couple. The land he will aquire will be registered as his private holding.

4. ወላጆቻቸዉን በሞት ያጡ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አቅመ-ደካሞች፣ ሴቶችና አረጋውያን በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ወይም ለመተዳደር የመረጡ ሆነው ሳለ ለዚሁ የሚያስፈልገው የእርሻ መሬት የሌላቸው ወይም ያነሳቸው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ይህንኑ በማግኘት ረገድ የቀደምትነት መብት ይኖራቸዋል።

4. Children who lost their parents, disables, weaklings, women and ageds, when to be found to engaged in or prefer to engage in an agricultural activity but has no plot or has scarcity, have priority right in aquiring.

5. የግል ባለሀብቶች የሚጠቀሙበት መሬት በሥራ ላይ ያለውን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በጠበቀ ሁኔታ ከክልሉ ከመንግሥት በሊዝ ውል ወይም ከማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ጋር በሚደረግ ስምምነት በኪራይ የማግኘት መብት አላቸው፣

5. Private investors have the right to aquire, in line with the land use plan from the regional government through lease contract or in rental agreement made with any rural landholder.

6. በክልሉ ውስጥ ሥራቸውን የሚያካሂዱ ወይም ለማኅበ-ረሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማትና የብዙኃን ማኅበራት ተግባራቸውን የሚያከናውኑት ለገንዘብ ትርፍ እስካልሆነ ድረስ የአርሶ-አደሮችን መሬት የማግኘት መብት በማይጻረር ሁኔታ ለተልዕኳቸዉ መሳካት የሚጠቀሙበት የገጠር መሬት ባለይዞታነት የማግኘት መብት አላቸው፡፡

7. ከዚህ በላይ በሰፈሩት ንዑስ አንቀጾች ስር ለተዘረዘሩት አካላት የገጠር መሬት ይዞታ የሚሰጥበት ስርዓት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

11.የገጠር መሬት በይዞታ ስለ ሚገኝባቸዉ ሁኔታዎችና ስለ ይዞታ ጣሪያ

በክልሉ ውስጥ ነዋሪ የሆነና በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም በዚሁ ሙያ ለመተዳደር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በሚከተለው አኳኋን የገጠር መሬት በይዞታ የማግኘት መብት አለው፡-

1. በመደበኛነት በሚኖርበት ቀበሌ መሬትን ከሚያስተዳድረው አካል በድልድል፤

2. በማናቸውም የክልሉ አካባቢ በውርስ ወይም በስጦታ፡፡

6. Governmental offices operating their work in the region or giving service to the community, non-governmental organizations, religious institutions and mass associations have the right of aquiring rural land to use for the achievement of their mission as far as it is not for the sake of profit and does not contradict with the farmers' right of acquiring land.

7. A rural land giving system for the stipulated bodies in the above sub-articles shall be determined by a regulation issued to implement this proclamation.

11. Conditions of Acquiring Rural Land through Holding and Ceiling of Holding

Any person residing in the region and engaged in agricultural activity or wants to engage in this activity has the right to aquire rural land through holding in the following conditions:

1. Through distribution from the kebele land administratoring body where he regularly resides

2. Through inheritance or donation in any area of the region.

12. ስለ ገጠር መሬት አሰጣጥ ስርዓትና የሚሰጠው መሬት ዝቅተኛ መጠን

1. የመሬት ጥያቄ የሚቀርብበትም ሆነ ምላሽ የሚሰጥበት ስርአት፣እንዲሁም አንድ ሰው የሚያገኘው የመሬት ስፋት ጣሪያ እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ መሬቱ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ተመስርቶ ይህንን አዋጅ በማስፈጸም ወደ ፊት በሚወጣ ደንብ ይደነገጋል።
2. የመሬት አሰጣጥ ስርአቱ እንደጠያቂዎቹ የመሬት ፍላጎት በህዝብ ተሳትፎ በሚወሰነው ቅደም ተከተል መሰረት መሬት በይዞታ የማግኘት መብት ላላቸው አመልካቾች ሁሉ ያለአድልዎ እንዲተገበር ይደረጋል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ስር የተደነገገው ቢኖርም ሊሰጥ የሚችለው የመሬት መጠን ችግሩ ላለባቸው ጠያቂዎች ሁሉ እኩል ሊዳረስ የማይችል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንደ ቅደም ተከተላቸው ወላጆቻቸዉን በሞት ላጡ ሕፃናት፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአቅመ ደካሞች፣ ለሴቶችና ለአረጋውያን ይሰጣል።
4. ለተጠቃሚዎች የሚሰጠው የመሬት መጠን በሚወሰንበት ጊዜ የመሬቱ ለምነት ደረጃና ሌሎች በደንብ የሚዘረዘሩ ታሳቢዎች ግምት ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል።

12. The Procedure of Rural Land Provision and the Minimum Amount

1. The land request as well as responding procedure and the ceiling of land one person aquires, based on the context of an area and the service the land gives shall be provided in a regulation that will be issued to implemet this proclamation.

2. The procedure of giving land based on the sequence of decision made by the public as per the land demand of applicants shall be implemented for all applicants without partiality to those who have the right of aquiring land through holding.

3. Notwithstanding the provision under sub-article /2/ of this Article, when it is found to be the will be givenland is not enough for all applicants equally, it is given for children who have lost their parents, disables, weaklings, women and ageds respectively.

4. During the time of deciding the area of land to be distributed, the level of fertility of land, and other assumptions to be stated in a regulation shall be considered.

5. ለአንድ ሰው የሚሰጠው በዝናብ ወይም በመስኖ የሚለማ የአንድ ማሳ አነስተኛ መጠን ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

13. ስለ ገጠር መሬት ሽግሽግ

1. ይህ አዋጅ ከሚጸናበት ቀን ጀምሮ በክልሉ ውስጥ በየትኛውም የገጠር አካባቢ የመሬት ሽግሽግም ሆነ ክፍፍል አይካሄድም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የሰፈረው ድንጋጌ በመስኖ የሚለማን መሬት ለተለያዩ ተጠቃሚዎች የማከፋፈልን ተግባር የሚከለክል አይሆንም።
3. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጠው ቢኖርም በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ በተገነቡ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ምክንያት መሬታቸውን ያጡ ባለይዞታዎች በመስኖ ተጠቃሚ ከሆኑ ሌሎች ወገኖች መሬት በክፍፍል እንዲያገኙ ይደረጋል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
4. በመስኖ ልማት ፕሮጀክት ምክንያት የሚካሄድን የገጠር መሬት ሽግሽግ ተከትሎ የመስኖ መሬት ክፍፍል በሚከናወንበት ጊዜ መሬታቸውን ያጡ ወይንም ይዞታቸው የተቀነሰባቸው ሰዎች ከተስተናገዱ በኋላ ትርፍ መሬት የተገኘ እንደሆነ መሬት የሌላቸው ወላጆቻቸዉን በሞት ያጡ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አቅመ ደካሞች፣ ሴቶችና አረጋዊያን መሬት በማግኘት ረገድ ከሌሎች ወገኖች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

5. The minimum plot of land, to be given to a person, developed by rain or irrigation will be determined by a regulation issued following this proclamation.

13. Rural Land Re-distribution

1. In any part of the region, land re-distribution and allotment shall not be carried out since the coming into force of this proclamation.
2. The provision listed under sub-article (1) of this Article does not prohibit the allotment of irrigation land to users.
3. Notwithstanding the presence under sub-article (1) of this Article, land holders displaced from their holdings due to irrigation development projects undertaken by the government or non-government organizations support, aquire land from other irrigation user parties through allotment. Particulars will be determined by a regulation.
4. Following a re-distribution of rural land due to irrigation development project, after those whose lands are subtracted are being treated at the time of irrigation land allotment, landless children who lost their parents, disables, weaklings, women and ageds are given priority in aquiring land when an extra land is found.

14. ስለ መሬት ድልድል

የገጠር መሬት ባለ ይዞታዎች በሕይወት የሌሉና ሕጋዊ ወራሽ የሌላቸው ሆኖ የተገኘ ወይም በሰፈራ ምክንያት ወይም በራሳቸው ፍላጎት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ከተወሰነው የጊዜ ገደብ በላይ አካባቢውን ለቀው የቆዩ ከመሆናቸው የተነሳ ነጻ መሬት መገኘቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ይኸው ትርፍ መሬት ለአካባቢው ነዋሪዎች በድልድል ይሰጣቸዋል።

15. ስለ ገጠር መሬት ኪራይ

1. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ራሱን ከይዞታው እስከማፈናቀል በማያደርስ ሁኔታ በያዘው መሬት የመጠቀም መብቱን ለሌላ ለማንኛውም ሰው በኪራይ ውል ማስተላለፍ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ሰው የይዞታ መብቱን ከግብርና ሥራ ውጭ ለሆነ ተግባር ማከራየት አይችልም።
3. ማናቸውም ዓይነት የገጠር መሬት ኪራይ ውል በጽሑፍ መደረግ ይኖርበታል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት የሚደረገዉ የመሬት ኪራይ ውል ስምምነት የመሬቱን ስፋት፣ የኪራዩን ዘመን፣ የክፍያውን መጠንና የአከፋፈሉን ሁኔታ በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት።
5. በውል የሚከራየው የገጠር መሬት በጋራ የተያዘ ከሆነ ሁሉም ባለይዞታዎች ካልተስማሙበት በስተቀር ውሉ ፈራሽ ይሆናል።

14. Land Distribution

When it is proved that free land is to be found, if the rural landholders are not alive and there is no legal heir or due to settlement or leaving their area by their consent longer than a deadline determined by a regulation issued to implement this proclamation, this extra land is given to the local residents through distribution.

15. Rent of Rural Land

1. Any rural landholder can transfer his land using right to any person through rent contract as far as it does not displace himself from his holding.
2. Notwithstanding the provision under sub-article /1/ of this Article, any person can not rent his holding right to any activity other than agriculture.
3. Any type of rural land rent contract should be made in written.
4. The contractual agreement of land rent according to sub-article (3) of this article, should clearly indicate area of the land, duration of rent, the rental amount and the way how the payment is made.
5. The contract will be invalid unless all landholders agree if the rural land to be rented in contract is held commonly.

6. በግል ባለይዞታዎች መካከል በሚደረግ የመሬት ኪራይ ውል ስምምነት የሚከፈለው የኪራይ መጠን አከራይና ተከራዩ በሚያደርጉት ድርድር የሚወሰን ይሆናል፡፡

7. በኪራይ ውል ስምምነቱ ውስጥ እንደገና የማከራየት መብት ያለው ስለ መሆኑ በግልፅ ካልተመለከተ በስተቀር ተከራዩ በውል ያገኘውን መሬት ለሶስተኛ ወገን መልሶ ሊያከራየው አይችልም፡፡

8. ማናቸውም የመሬት ኪራይ ውል ስምምነት እስከ ሁለት ዓመት ለሚዘልቅ ጊዜ የተደረገ ከሆነ መሬቱ ለሚገኝበት ቀበሌ አስተዳደርና ከዚያ ለበለጠ ጊዜ የተደረገ ከሆነ ደግሞ ለወረዳው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

9. በዚህ አዋጅ መሠረት ከፍተኛው የገጠር መሬት ኪራይ ውል ዘመን ቋሚ የፍራፍሬ ተክሎችን ወይም የተመረጡ የዛፍ ዝርያዎችን የተመለከተ እንደሆነ 30 ዓመት ሲሆን ዓመታዊ ሰብሎችን የተመለከተ ከሆነ ደግሞ 10 ዓመት ይሆናል፡፡ ስለሆነም እንደተገቢነቱ ከ30 ዓመት እና ከ10 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ተደርጎ የተገኘ የመሬት ኪራይ ውል ስምምነት ቢኖር በዚህ አዋጅ መሰረት እንደቅደም ተከተላቸዉ ለ30 ዓመት እና ለ10 ዓመት እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

6. The amount of rent to be paid will be determined by the bargain made by the rentier and the renter in the contractual agreement of land entered between private landholders.

7. The renter can not transfer the land he got through rent contract to a third party unless it is clearly indicated the right of re-rent in the rent contract agreement.

8. Any land rent contractual agreement upto the period of two years should be registered being presented to the kebele administration where the land is found and to the office of the rural land administration and use when the agreement is longer than the period of two years. Details will be determined by a regulation.

9. The maximum period of rural land rent, based on this proclamation, is 30 years concerning to permanent fruit plants or preferred tree types, and 10 years concerning annual crops. Hence, as its appropriateness, an agreement to be found more than 30 and 10 years is presumed as for 30 and 10 years respectively in accordance with this proclamation.

10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) ስር የተመለከተው ከፍተኛው የኪራይ ዘመን ጣሪያ መወሰኛ ድንጋጌ የውሉ ዘመን ሲያበቃ እንደገና ሊታደስ የሚችልበትን እድል የሚዘጋ አይሆንም፡፡

11. የኪራይ ዉል ስምምነቱ ሕጋዊ የዉል ማቋቋሚያ ሁኔታዎችን አሟልቶ ካልተገኘ ወይም ተከራዩ በተከራየዉ መሬት ላይ ጉዳት ካደረሰ ወይም ከስምምነታቸው ዉጭ ፈጽሞ ከተገኘ ዉሉ ፈራሽ ይሆናል፡፡

12. በሕጋዊ አሳዳሪ ወይም በሞግዚት ጥበቃ ስር የሚተዳደሩ ሕፃናት፣ አረጋዊያንና በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች ወይም የአእምሮ መታወክ ያለባቸው ስለመሆኑ በፍርድ የተረጋገጠላቸው ባለይዞታዎች የመሬት ይዞታቸውን ሲያከራዩ ውሉ የእነርሱን ጥቅም በማይጎዳ ሁኔታ ስለመደረጉ ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ የቤተ-ዘመድ ጉባኤ የመከረበትና ውል ለመዋዋል ሥልጣን የተሰጠው አካል ያጸደቀው ሰነድ ከኪራይ ውሉ ጋር ተያይዞ ለምዝገባ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

10. The maximum rent period ceiling determination provision indicated under sub-article (9) of this Article does not deprive a chance of renewing when the the contract period ends.

11. The rent contractual agreement becomes invalid if it does not fulfill the legal requirements of the contract or when the renter found to commit damage on the rented land or implemented contrary to their agreement.

12. The document that the authorized body to make a contract has approved after being discussed by a family council should be presented with the rent contract so as to ensure that the agreement should not harm the benefit of them when the children under the protection of guardians or tutor, ageds and interdicted persons or persons whose insanity is adjudged by court holders rent their land.

16. ስለ ስጦታ

1. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ የይዞታም ሆነ የመጠቀም መብቱን በክልሉ ዉስጥ ለሚኖርና ከዚህ በታች ከተመለከቱት መመዘኛዎች መካከል ቢያንስ አንዱን ለሚያሟላ ሰዉ በስጦታ ማስተላለፍ ይችላል፡-

16. Donation

1. Any rural landholder can transfer the landholding as well as his use right to any person residing in the Region and for whom fulfills atleast one of the following criterion through donation:

ሀ. ከፍተኛውን የይዞታ ጣሪያ እስካላለፈ ድረስ በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚህ ሙያ መተዳደር ለሚፈልግ ልጅ ወይም የልጅ ልጅ ወይም ለማንኛውም ሌላ የቤተ-ሰብ አባል፤

ለ. መረጃውን በጽሑፍ አረጋግጦ እስከሰጠ ድረስ በወቅቱ እየጦረው ላለና አገልግሎኛል ወይም እያገለገለኝ ነው ብሎ ላመነው በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ ሥራ መተዳደር ለሚፈልግ ሌላ ማንኛውም ሰው፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ ቁጥር (ለ) መሠረት የሚደረገው ስጦታ ሊጸና የሚችለው ስጦታ ተቀባዩ ባለይዞታውን በመጦር ላይ ያለ ወይም ሲንከባከብ የቆየ ስለመሆኑ "በቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤት" በኩል በጽሑፍ አረጋግጦ ሲቀርብ ብቻ ይሆናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር የተደነገገው ቢኖርም ባለይዞታው ያደረገው ስጦታ አካለ-መጠን ያልደረሱ ልጆቹን ወይም ሌሎች የቤተ-ሰብ አባላትን መብት ሙሉ በሙሉ በሚጎዳ ወይም ለነርሱ በቂ ድርሻ በማያስቀር ሁኔታ የተከናወነ ከሆነ በሕግ ፊት ተቀባይነት አይኖረውም።

A. To a child or grandchild or any other family member who engaged in agricultural activity or wants to engage in this activity as far as it does not exceed the maximum ceiling of holding.

B. To any other person who engaged in agricultural activity or wants to engage in this activity that the landholder belives he has served or has been serving him as far as the landholder gives the document approving in written.

2. The donation made in accordance with under letter (B), sub-article (1) of this Article shall be effective if and only if the donee presents a written approval by the kebele social court about his caring or has been caring the donor.

3. Notwithstanding the provision under sub-article (1) of this Article, a donation made by a landholder is invalid if it is made in a way that harms totally his minor children or other family members or not leaving enough shares to them.

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ-ቁጥሮች ሀ እና ለ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ይዞታውን ቀድሞውኑ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ለሌላቸው ሰዎች መስጠት ወይም በማናቸውም ዘዴ ማስተላለፍ አይችልም፡፡

4. Notwithstanding the provision under sub-article (1)_ letters A and B of this Article, any rural landholder can not give or transfer his holding in any method for those who have no right of use of the rural land in advance.

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ የይዞታ መብቱን በቋሚነትና የመጠቀም መብቱን ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ ለተለያዩ ሰዎች በስጦታ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

5. Without prejudice to the provision under sub-article (1) of this Article, any rural landholder can transfer his holding right permanently and his using right for a limited period of time for different persons.

6. የመሬት ይዞታው በባልና ሚስት ወይም በሌሎች ሰዎች በጋራ የተያዘ ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ የጋራ ይዞታ ለማስተላለፍ የተደረገው የስጦታ ውል የሚጸናው ባልና ሚስቱ ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የጋራ ባለይዞታዎች ሁሉም ከተስማሙበት ብቻ ይሆናል፡፡

6. If the landholding is held by spouse or other persons commonly, the contract made to transfer this donation shall be effective only when the spouses or the concerned bodies of the common holders agreed all.

7. ማንናቸውም የስጦታ ውል ስምምነት በጽሑፍ መደረግ አለበት፣ በቃል የተደረገ የስጦታ ዉል ስምምነት በሕግ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

7. Any contract of donation should be in written; a contract donation agreement made in verbal shall not have accepetance before the law.

8. በጽሑፍ የተደረገ ማንኛውም የስጦታ ዉል ስምምነት መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ላለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ቀርቦ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

8. Any contract of donation made in written be submitted and registered in the wereda rural land administration and use office where the land is found.

9. ውሉ አግባብ ላለው የወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ቀርቦ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል::

9. The contract will be effective since the date of registration by the pertinent wereda rural land administration and use office.

10. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /9/ ስር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለ ይዞታውን ለመጦር መሬቱን በስጦታ የተቀበለ ማንኛውም ሰው በገባው ውል መሰረት ሰጪውን አለመጦሩ የተረጋገጠ እንደሆነ ሰጪዉ ጉዳዩን ወደ መደበኛ ፍርድ ቤት በማቅረብ ውሉ እንዲፈርስለት የመጠየቅ መብት አለዉ፡፡

17. ስለ ውርስ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የገጠር መሬት ባለይዞታ የሆነ ማንኛውም ሰው የይዞታም ሆነ የመጠቀም መብቶቹን በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ ሙያ መተዳደር ለሚፈልግ ማንኛውም ሌላ ሰው በኑዛዜ ሊያስተላለፍ ይችላል፡፡
2. ባለይዞታው የይዞታና ለተወሰነ ጊዜ ደግሞ የመጠቀም መብቶቹን ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች በኑዛዜ ሊያስተላልፍ ይችላል::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና (2) ስር የተደነገገው የይዞታና የመጠቀም መብቶችን በኑዛዜ የማስተላለፉ ተግባር አካለ-መጠን ያላደረሰውን የተናዛዡን ልጅ ከህጋዊ ወራሽነት መብቱ የሚነቅል ወይም የተናዛዡን የትዳር ጓደኛ ሕጋዊ መብት የሚጎዳ ሆኖ የታየ እንደሆነ በሕግ ፊት የሚጸና አይሆንም፡፡
4. የኑዛዜ አደራረግ “በፍትሀ-ብሄር” ሕግ ውስጥ እንደተደነገገው በግልጽ የሚካሄድ ኑዛዜ የሚሰጥባቸውን መስፈርቶች ማሟላትና አግባብ ላለው የወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ ይኖርበታል፣

10. Without prejudice to the provision under sub-article /9/ of this Article, when it is proved that any donee to care for is not caring the maintenance-creditor in accordance with his promise, the maintenance-creditor has the right to seek the invalidation of the contract by submitting the issue to the regular court.

17. Inheritance

1. In accordance with this proclamation, any person who is the ruralholder land may transfer his holding as well as use right to any person engaged in agricultural activity or to any other person who wants to engage in this activity through will.
2. The landholder can transfer his holding and using right for specific time for more than one person through will.
3. The act of transferring the holding and use right, provided under sub-articles /1/ and /2/ of this Article shall be invalid if it disinherits the legal heirship of the testator’s minor children or harms the legal rights of his spouse.
4. Making will shall meet the criteria of public will clearly mentioned in the Civil-Code, and should be submitted and registered by the pertinent wereda land administration and use office.

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና (2) ስር የተደነገገው ቢኖርም ባለይዞታው በኑዛዜ ሳያወርስ የሞተ ወይም የሰጠው ኑዛዜ ፈራሽ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ መብቱ እንደ ቅደም ተከታላቸው በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ ሥራ መተዳደር ለሚፈልግ የሟች ልጆች፣ ወላጅ/ጆች ወይም ሕግ ለሚፈቅድለት ለማንኛውም ሌላ የቤተ-ሰቡ አባል ይተላለፋል፡፡

5. Notwithstanding the presence of the provision provided under sub-articles /1/ and /2/ of this Article, when one is found intestate or the given will is to be void, the right is transferred to deceased children, parent/parents or to any legally permitted other family member respectively who engaged in or wants to engage in agricultural activity.

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ስር ከተጠቀሱት የሟች ልጆች ወይም ከልጆቹ አንዱ ቀድመዉ ሞተዉ ወይም ሞቶ እንደሆነና ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ትተዉ/ትቶ እንደሆነ እነዚሁ ተወላጆቻቸዉ የሚቹ የቤተ-ሰብ አባል ሆነዉ ተገኝተዉ ካልወረሱ በስተቀር ቀድመዉ በሞቱት ልጆች ምትክ ሆነዉ እንዲወርሱ ይደረጋል፡፡

6. If the deceased children or one of them mentioned under sub-article 5 of this Article are predeceased and left their descendants, the grand children inherit representing the predeceased unless these descendants inherit being a family member earlier.

7. ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ሕፃናት በጋብቻ ውስጥም ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ መሆናቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ የገጠር መሬት ይዞታን በመውረስ ረገድ እኩልና ያለ ልዩነት ይስተናገዳሉ::

7. The children who lost their parents are equally treated in bequeathing the rural landholding regardless of being born in wedlock or out of wedlock.

8. ማንኛውም ሰው ሳይናዘዝ በሞተበት ወቅት በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም ለመተዳደር የሚፈልግ ወደ ታች የሚቆጠር ተወላጅ የሌለው ሆኖ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ወይም ለመተዳደር የሚፈልጉ ወላጅ/ጆች ካለው ወይም ካሉትና አስቀድሞ ያላቸው የገጠር መሬት ይዞታ መጠን ከከፍተኛው የይዞታ ጣሪያ በታች መሆኑ የታወቀ እንደሆነ የመሬት ይዞታውን እነርሱ የመውረስ መብት ይኖራቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል::

8. When any person found intestated and has no descendant whose livelihood is agriculture or wants to engage in this activity, parent/parents (if there is/there are) has the right to inherit if they engaged in or want to engage in agricultural activity when it is known that their previous land they have is not exceeding the ceiling of holding. Particulars will be determined by a regulation.

9. ከአንድ በላይ የሆኑ ወራሾች በውርስ ያገኙትን የገጠር መሬት በሚከፋፈሉበት ጊዜ የእያንዳንዳቸው ድርሻ በደንቡ ከተወሰነው የአንድ ማሳ አነስተኛ መጠን በታች ሆኖ የተገኘ እንደሆነ መሬቱን በጋራ መጠቀም እንጅ መከፋፈል አይችሉም።

10. በዚህ አንቀጽ ከዚህ በላይ በሰፈሩት ድንጋጌዎች መሠረት ወራሽ ያልተገኘለት የትኛውም የገጠር መሬት ይዞታ ወደ መሬት ባንክ ገቢ ተደርጎ ለአዲስ አመልካቾች እንዲከፋፈል ይደረጋል፣

11. መደበኛ ነዋሪነታቸውን የመሠረቱት ከገጠሩ አካባቢዎች ጋር በሚዋሰኑ ከተሞች ውስጥ ሆኖ ዝቅተኛ ገቢ በሚያስገኝ ሌላ ቋሚ ሥራ ላይ ተሰማርተው ሳለ ኑሯቸውን ገጠር ውስጥ ከሚከናወን የግብርና ሥራ በሚመነጭ ገቢ የሚደጎሙ ሰዎች ለውርስ ዓላማ ሲባል በዚህ አዋጅ መሠረት እንደ አርሶ አደር ይቆጠራሉ።

18. የገጠር መሬት ይዞታን ከግል ባለሃብት ጋር በጋራ ስለማልማት

1. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ የመጠቀም መብቱን እንደያዘ ከግል ባለሀብቱ ጋር በጽሑፍ ተዋውሎ ይዞታውን በጋራ የማልማት መብት ይኖረዋል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተደረገ ውል አግባብ ላለው የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ቀርቦ መመዝገብ አለበት።

9. When it is found that the share of each heir is less than the minimum amount of farm, determined by the regulation, at the time of division by more than one heirs_they can not divide the farm instead they use commonly.

10. Based on the above provisions within this article, any rural landholding which has no heir will be distributed to new applicants after being submitted land bank.

11. For the sake of inheritance objective, in this proclamation, persons residing permanently in towns bordering with the rural areas who engaged in permanent job_earning least income but support their living on an icome generated from the rural land are considered as farmers.

18. Developing Rural Land Jointly with a Private Investor

1. Any rural landholder has the right to develop his landholding jointly with a private investor making contract in written. Details will be determined by a regulation.

2. The contract, made in accordance with sub-article (1) of this Article, should be submitted to and registered by a pertinent wereda rural land administration and use office.

19. በመሬት የመጠቀም መብትን የብድር ዋስትና አድርጎ ስለማስያዝ

1. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ በዚህ አዋጅ ከተፈቀደው ከ30 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የመጠቀም መብቱን በሀገሪቱ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ለተሰጠው ሕጋዊ የገንዘብ ተቋም የብድር ዋስትና አድርጎ ሊያስይዝ ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
2. ተበዳሪው በብድር ውሉ ውስጥ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ዕዳውን ያልከፈለ እንደሆነ አበዳሪው በብድር ውሉ ለተጠቀሰው ጊዜ በመሬቱ የመጠቀም መብት የሚኖረው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የዚሁ መብቱ ወሰን በመሬቱ ላይ ከተሰጠው የመጠቀም መብት ያለፈ ሊሆን አይችልም።
3. አበዳሪው መሬቱን ራሱ የማያለማውና ከዚሁ የተነሳ ለሶስተኛ ወገን በኪራይ የሚያስተላልፈው ከሆነ መሬቱን ከአበዳሪው በውል ለመውሰድ እስከ ተስማማ ድረስ ተበዳሪው ቅድሚያ ይሰጠዋል።
4. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት መያዣ የተደረገበት ማንኛውም ውል ባበዳሪዉ ተቋም መመዝገብ አለበት፤ ይኸው የተመዘገበው የኪራይ ውል አንድ ቅጅ መሬቱ ለሚገኝበት ወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ቀርቦ ከባለይዞታው የግል ማህደር ጋር መያያዝ ይኖርበታል።

19. Mortgaging Land Use Right

1. Any rural landholder may martgage his using right to financial institution which has given recognition by the country's National Bank for not more than 30 years permitted by this proclamation. Details will be determined by a regulation
2. When the borrower is unable to return his debt within the period of time indicated in the loan contract and if the lender is found to be served by the land for the period of time specified in the loan contract; the scope of the right can not exceed the right of use.
3. If the lender does not develop the land by himself and transfers to a third party through rent as a result of this, the borrower is given priority as far as he agreed to take the land in contract from the lender.
4. Any contract of mortgage related to rural land use right should be registered by the the lender institution; the copy of this rent contract should be attached with the landholder's personal file being submitted to the wereda rural land administration and use office where the land is found.

20. ይዞታን ስለመለዋወጥ

1. ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ ማሳዉን በቀበሌዉ ወይም በሌላ ቀበሌ ውስጥ ከሚገኝ ሌላ ባለይዞታ ጋር መለዋወጥ ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
2. አነስተኛ ማሳዎች ለልማት አመቺ ይሆኑ ዘንድ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች በተናጠል ይዞታዎታቸውን ኩታ ገጠም ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት ሊያደርጉ ይችላሉ።
3. ከዚህ በላይ በሰፈሩት ድንጋጌዎች መሠረት በባለይዞታዎች መካከል የሚደረግ ማናቸውም የልውውጥ ውል አግባብ ላለው የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ቀርቦ መመዝገብ አለበት።
4. መሬቱ የባልና ሚስት የጋራ ይዞታ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ባለይዞታዎች በጣምራ የተያዘ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ልውውጡ በሁሉም ባለይዞታዎች ፈቃድ ላይ ተመስርቶ መፈጸም ይኖርበታል።
5. የተናጠል ይዞታዎቻቸውን ኩታ ገጠም ለማድረግ አስበው የገጠር መሬት ልውውጥ ለሚያደርጉ ባለይዞታዎች የተለየ ማበረታቻ ይሰጣቸወል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

21. የይዞታ መብት ስለሚታጣባቸው ሁኔታዎች

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 /3/ ስር የተደነገገው ቢኖርም በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለው ማንኛውም ባለይዞታ ይዞታውን በሚከተሉት ምክንያቶች እንዲያጣ ሊወሰን ይችላል፡-

20. Holding Exchange

1. Any rural landholder can exchange his plot with another landholder found either in the kebele or in other kebele. Particulars will be determined by a regulation.
2. Rural landholders may make an agreement on their holdings individually so as to make small plots adjoint and suitable for development.
3. Any contract of exchange made between and among landholders, in accordance with the provisions above, should be submitted to and be registered by the pertinent wereda rural land administration and use office.
4. The exchange should be implemented based on the consent of all landholders if the land is found to be held by spouses or more than one landholder in common.
5. Special incentive is given for those who make rural land exchange_thinking to make adjacent their holdings. Particulars will be determined by a regulation.

21. Conditions of Deprivation of Holding Right

1. Notwithstanding the provision under Article 5 /3/ in this proclamation, it may be decided that any landholder having the right to use the rural land may be deprived of his holding in the following reasons:

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 (2) ፊደል ተራ ቁጥር (ለ) ሥር አስቀድሞ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በግል፣ በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅት ወይም በሌላ በማናቸውም ተቋም ሥራ ላይ ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ቋሚ ባልሆነ መንገድ ተቀጥሮ መገኘት፤

A. without prejudice to the provision provided under Article 7 (2) letters (B) of this proclamation, being found to be employed in a private, government or non-governmental organization or in any work of another institution for indefinite time or in any way which is not permanent;

ለ. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ ይዞታውን ለሶስተኛ ወገን ማከራየቱን ወይም የሚያስተዳድርለት ሰው መመደቡን መሬቱ ለሚገኝበት ወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ሳያሳውቅ በተከታታይ ለ5 ዓመታትና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ከመኖሪያ አካባቢው መጥፋት ወይም ወደ ውጪ አገር ሂዶ መገኘት፤

B. the detail being determined by a regulation, being disappeared from his area of residence or being found gone to abroad for the consequetive five years and above without notifying the rent of his holding to a third party or assigning a person to administer his land to the pertinent wereda land administration and use office where the land is being found;

ሐ. የመሬት ይዞታው ለሕዝብ አገልግሎት ይውል ዘንድ አግባብ ያለው አካል የሚያሳልፈው ውሳኔ፤

C. the decision passed by a pertinent body so as to use the land for public service;

መ. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ መሬቱን ያለበቂ ምክንያት እስከ ሦስት ዓመት ለዘለቀ ጊዜ ጦም አሳድሮ መገኘት፤

D. details being determined by a regulation, being found to make the land idle upto 3 years without justifiable cuases;

ሠ. ዝርዝሩ በደንብ የሚወሰን ሆኖ ይዞታውን በተዘጋጀው የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት አለማልማትና ይኸው ዕቅድ ባልተዘጋጀላቸዉ አካባቢዎች ደግሞ መሬቱን በእንክብካቤ ካለመያዙ የተነሳ ከባድ ጉዳት አድርሶ መገኘት፤

E. details being determined by a regulation, not developing the holding according to the prepared land use plan and in areas where this plan is not yet prepared, being found to cuase a serious damage on the land due to mal treatment;

ረ. የመሬት ይዞታ መብቱን በራሱ ፈቃድ የተወ ስለመሆኑ አግባብ ላለው ወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት በጽሁፍ አሳውቆ መገኘት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር በተደነገገው መሠረት የገጠር መሬት ይዞታውን በማናቸውም ምክንያት እንዲያጣ የተደረገ ማንኛውም ሰው በመሬቱ ላይ ላለማው ቋሚ ንብረት ተገቢውን ካሣ በቅድሚያ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተደነገገው ቢኖርም አስቀድሞ የተሰማራበት ቋሚ መተዳደሪያ የግብርና መስክ ሆኖ ሳለ በጥረቱ ተጨማሪ ሀብት መፍጠርና ከዚሁ የተነሳም ወደ ኢንቨስትመንት ሥራ ለመሸጋገር የበቃ ማንኛውም ታታሪ አርሶ-አደር ለግብርና ሥራ የተሰጠውን የገጠር መሬት ይዞታ በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲያጣ አይደረግም፡፡

F. When he has left his landholding right in his consent by notifying the pertinent wereda land administration and use office in written form.

2. According to the provision made under sub-article 1 of this Article, any person deprived of his rural landholding right for any reason has the right to get commensurate compensation in advance for the permanent property he has produced on the land.

3. Notwithstanding the provision under sub-article /1/ of this Article, any industrious farmer being transferred to investment work due to creating additional income while his permant levilihood is agriculture shall not be deprived of his given plot for agricultural work_ in accordance with this proclamation.

22. የገጠር መሬትን በግብርና ኢንቨስትመንት ስም ለግል ባለሀብቶች በሊዝ ስለማስተላለፍ

1. በየትኛውም ዓይነት የግብርና ኢንቨስትመንት ተግባር ለመሰማራት የሚፈልጉ የግል ባለሃብቶች ለዚሁ ዓላማ የሚያስፈልገውን የገጠር መሬት በጨረታ ተወዳድረው ሊያገኙ ይችላሉ፣

2. የግል ባለሀብቶች ለሚያቀርቡት የመሬት ጥያቄ ምላሽ የሚሰጠው በመካከላቸው ግልጽ ውድድር እንዲካሄድ በማድረግ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

22. Transferring Rural Land to Private Investors in the Name of Agricultural Investment through Lease

1. Private investors who want to engage in any kind of agricultural investment activity may aquire rural land, needed for this objective, competing in tender.

2. The land request presented by private investors is responded by making a public competition between and among them. Detail will be determined by a regulation.

3. ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት በሚካሄድባቸው የክልሉ አካባቢዎች የብሎኪንግ ወይም የረድፍ አሠራር ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

3. The blocking or column system is being functional in areas of the region where wide agricultural investment is takenplace. Particulars will be determined by a regulation.

4. ለሰብል ልማት አገልግሎት ሊውል የማይችል የትኛውም የገጠር መሬት የአጠቃቀም ዕቅዱ በሚፈቅደው መሠረት በኢንቨስትመንት ተካቶ ለተስማሚ የግብርና ደን ልማት ሥራ እንዲውል ይደረጋል፡፡

4. Any rural land which will not be used for cereal development in any area will be made for suitable agricultural forest being included in investment based on the rural land use plan.

5. በሊዝ የተገኘን የገጠር ኢንቨስትመንት መሬት ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የግል ባለሃብቶች በዚህ አዋጅና አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕግጋት፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ተስማምተው በጋራ ሊያለሙት ይችላሉ፡፡

5. Two or more private investors, based on this proclamation and other pertinent laws, regulations and directives, may develop jointly_ being agreed, the rural investment land found in lease.

6. ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚውል የገጠር መሬት ከፍተኛ የሊዝ ዘመን 30 ዓመት ይሆናል፡፡ ስለሆነም ከ30 ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ ተደርጎ የተገኘ የገጠር መሬት ሊዝ ስምምነት ቢኖር በዚህ አዋጅ መሠረት ለ30 ዓመት እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡ የዉል ዘመኑ ሲያበቃም ውል እንደገና ሊታደስ ይችላል፡፡

6. The maximum lease year of rural land which will be used for agricultural investment shall be for 30 years. Hence, if there is any rural land lease made for more than 30 years, it is presumed as for 30 years in accordance with this proclamation. A contract may be renewed when the duration of the contract is over.

23. ከግብርና ኢንቨስትመንት ውጭ የሚውል የገጠር መሬት በሊዝ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

23. A Condition of Providing Rural Land Other than Agricultural Investment through Lease

1. ከግብርና ኢንቨስትመንት ውጭ ለሆኑ ሌሎች ተግባራት በገጠር መሬት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ጥያቄ የሚያቀርቡ የግል ባለ ሀብቶች ሲኖሩ የፕሮጀክት ፍላጎታቸው በተናጠል እየታየ የጠየቁትን መሬት በግልጽ በሚካሄድ የሊዝ ውድድር ሊያገኙ ይችላሉ፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይደነገጋል፡፡

1. When there are private investors request to invest on the rural land other than agricultural investment, they may aquire the land they requested through public lease tender competition being their project need is evaluated individually; details will be provided by a regulation.

24.ከግብርና ውጭ ለሆነ የገጠር መሬት ኢንቨስትመንት የሚደረገው የሊዝ ውል ዘመን ጣሪያ 60 ዓመት ይሆናል።

24. በሊዝ ስርዓት የተገኘን በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የዕዳ ዋስትና አድርጎ ስለማስያዝ እና ለሶስተኛ ወገን ስለማስተላለፍ

1. የገጠር መሬትን በሊዝ የወሰደ ማንኛውም የግል ባለሃብት የሊዝ ውሉ ጸንቶ ለሚቆይበት ጊዜ በተከራየው መሬት ላይ ያለውን የመጠቀም መብት ወይም በመሬቱ ላይ ያፈራውን ሃብት ወይም ሁለቱንም የዕዳ ዋስትና አድርጎ ለማስያዝ ይችላል::

2. በውሉ ውስጥ ይህንኑ የሚቃረን ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በመሬት የመጠቀም መብቱ የዕዳ ዋስትና ሆኖ ከተያዘ በመሬቱ ላይ የለማው ሀብትም አብሮ እንደተያዘ ይቆጠራል። ሆኖም በመሬቱ ላይ የለማው ሀብት ተነጥሎ በዕዳ ዋስትናነት የሚያዝ ሲሆን በመሬት የመጠቀም መብቱም ሆነ ያለማዉ ኃብት ያረፈበት መሬት አብሮ እንደተያዘ ሊቆጠር አይችልም።

2. The maximum lease contract year on the rural land other than agricultural investment shall be 60 years.

24. Mortgaging and Transfering Rural Land Use Right Aquired through Lease System to Third Party

1. Any private investor that has taken the rural land through lease may mortgage the using right on his rent land or a property he produced on the land or both to debt for the duration of the effective date of the contract.

2. Unless there is a contrary provision in the contract to this, according to sub-article (1) of this Article_the property produced on the land is presumed as it is heldwith if the land using right is mortgaged. But when the property developed on the land is specifically mortgaged, the land using right as well as the land on where the developed property is located may not be presumed as heldwith.

3. የዕዳ ዋስትና ሆኖ የተያዘን በመሬት የመጠቀም መብት ባለገንዘቡ አስቀድሞ በጽሑፍ ካልተስማማ በስተቀር የአበዳሪውን ጥቅም በሙሉ ወይም በከፊል በሚጎዳ ሁኔታ በኪራይ ማስተላለፍ ወይም በሌላ በማናቸውም የመሬት ይዞታ መለወጥ አይቻልም።

4. በዚህ አዋጅ መሠረት በመሬት የመጠቀሙ መብት ወይም በመሬቱ ላይ የለማው ሃብት የዕዳ ዋስትና ሆኖ ሊያዝ የሚችልበት ጊዜ ገደብ በዉሉ ከተገለፀዉ የሊዝ ዘመን ሊበልጥ አይችልም።

5. በመሬት የመጠቀም መብትን በዕዳ ዋስትናነት የማስያዙ ውል ስምምነት በጽሑፍ መደረግ ይኖርበታል፤ በጽሑፍ ያልተደረገ እንደሆነ ዉሉ ፈራሽ ይሆናል። የስምምነቱ መግለጫ ሰነዱም መሬቱ ባለበት ወረዳ ለሚገኘው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ በስተቀር በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብባቸው አይችልም።

6. ለግብርናም ሆነ ለሌላ ለማናቸውም የኢንቨስትመንት ተግባር ይውል ዘንድ በሊዝ በተወሰደ የገጠር መሬት ላይ ያለ የመጠቀም መብት ውል ተቀባዩ ሳይናዘዝ የሞተ እንደሆነ ውሉ ጸንቶ ለሚቆይበት ጊዜ ለባለይዞታው ሕጋዊ ወራሾች በውርስ ሊተላለፍ ይችላል፤ ሆኖም ወራሾቹ ይህንን የመጠቀም መብት ሳይከፋፈሉ እንዲጠቀሙበት ይገደዳሉ።

3. It is impossible to transfer the land using right, held to be for debt, through rent or to exchange by any other land holding in conditions_ harming the benefit of the lender either totally or partially unless he expressed his prior consent in written.

4. According to this proclamation, the deadline of holding the land using right or the property developed on the land to be mortgaged can not exceed the duration of the lease indicated in the contract.

5. The contract of mortgage agreement relating to the land using right should be in written; lest the contract becomes invalid. Unless the agreement document is submitted to and be registered by the wereda rural land administration and use office where the land is found, it is impossible to be raised as objection against third parties.

6. The using right on the rural land taken for agriculture as well as for any investment function through lease may be transferred to the legal heirs of the landholder in inheritance for the effective date of the contract if the contract receiver is intestated. However, the heirs are obliged to use this right without dividing among themselves.

7. ባልና ሚስት በጋራ እየተጠቀሙበት የሚገኝ የኢንቨስትመንት መሬት በፍች ወቅትም ሆነ ከዚያ በኋላ የጋራ ይዞታቸው እንደሆነ ይቀጥላል እንጂ ለቀድሞ ተጋቢዎች አይከፋፈልም፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /6/ ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በላይ የሰፈረው የንዑስ አንቀጽ /7/ ድንጋጌ በሊዝ የተገኘንና በሌሎች ሰዎች በጋራ የተያዘን የገጠር መሬት አስመልክቶ በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
9. የክልሉ መንግሥት ለኢንቨስትመንት ይውል ዘንድ ለግል ባለሀብቶች በሊዝ የተሰጠን የገጠር መሬት ለላቀ የሕዝብ አገልግሎት በፈለገው ጊዜ ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ ከፍሎ ለመውሰድ ይችላል፡፡

25. ለግል ኢንቨስትመንት በተሰጠ የገጠር መሬት ላይ ሰለተጣለ ገደብ

1. ማንኛውም የግል ባለሀብት አግባብ ካለው አካል የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ መሬቱን አስፋፍቶ መያዝ፣ አስቀድሞ ከጸደቀለት ፕሮጀክት ዓላማ ውጭ መሬቱን ለሌላ ተግባር አውሎ መገኘት ወይም ለሶስተኛ ወገን ማከራየት አይችልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ(1) ስር ከተደነገገው ውጭ በሆነ አሰራር መሬቱን ለሶስተኛ ወገን አስተላልፎ የተገኘ ማንኛውም የግል ባለሃብት ያለአንዳች ቅድመ-ሁኔታ ውሉ ተሰርዞ መሬቱን እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

7. Investment land being commonly used by spouses shall not divided between the spouses rather it continues being as a common at the time of divorce as well as after.
8. Without prejudice to the provision under sub-article /6/ of this Article, the provision put under sub-article /7/ above shall apply the same concerning the land held by other persons commonly obtained in the form of lease.
9. The regional government can take the rural land given to private investors through lease for investment_paying a commensurate compensation in advance when it needs for greater public service.

25.The Limit Imposed on Rural Land Given for Private Investment

1. Any private investor can not expand his landholding without getting a written permission from a pertinent body; being found to used the land for another purpose other than the permitted in advance or rent to a third body.

2. Any private investor who is found transferred the land to a third body without observing the provision under sub-article (1) of this Article, the land is made to be returned _ being the contract canceled, without ay precondition.

26. የገጠር መሬት ይዞታን ለሕዝብ አገልግሎት ስለ ማስለቀቅ

1. የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት የገጠርን መሬት ለህዝብ አገልግሎት ለማዋል አስፈላጊ ሁኖ ሲያገኘው ከማንኛውም ባለይዞታ ወይንም ተጠቃሚ ተገቢውን ካሳ በቅድሚያ በመክፈልና ተፈናቃዩ በዘላቂነት የሚቋቋምበትን አማራጭ በማመቻቸት ለማስለቀቅ ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡
2. ለሕዝብ አገልግሎት እንዲውል የተፈለገ የገጠር መሬት ይዞታ እንዲለቀቅ የወረዳው አስተዳደር ጽህፈት ቤት ከመወሰኑ በፊት መሬቱ የሚለቀቅበት ፕሮጀክት ከአካባቢው ኅብረተሰብ ልማት ጋር በቀጥታ የተቆራኘ በሆነ ጊዜ ጉዳዩ ለቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ውይይት ቀርቦ የብዙኃኑን ድጋፍ ማግኘት ይኖርበታል፡፡
3. የወረዳ አስተዳደር ጽህፈት ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የገጠር መሬት ይዞታ በሕዝብ አገልግሎት ስም እንዲለቀቅ ሲወስን ከገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት የሚያገኘውን መረጃ ታሳቢ አድርጎ መሬት የሚለቀቅበትን ጊዜ ገደብና ለሚነሳው ንብረት የሚከፈለውን የካሳ መጠን በመግለጽ ለባለ ይዞታው ወይም ለተጠቃሚው በጽሑፍ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት፡፡
4. ባለይዞታው ወይም ተጠቃሚው በቀረበለት የካሳ መጠን ቅር የተሰኘ እንደሆነ አቤቱታውን በሕግ ለተቋቋመው የካሳ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ የማቅረብና የማስመርመር መብት ይኖረዋል፡፡

26. Expropriating Rural Land for Public Service

1. When it found necessary to use the rural land for public service, the wereda administrative office may expropriate any rural landholder or user by paying commensurate compensation in advance and facilitating alternatives that the displaced can be re-settled sustainably. Details will be determined by a regulation.
2. Before the wereda administrative office decides the land needed for public service to be taken, the project the land is being left should get the majority support being submitted to the resident population when the project is found to be directly related to the development of the local society.
3. When the wereda administration office decides the rural landholding is to be taken in the name of public service according to sub-article (1) of this Article, it has a responsibility to notify the time limit of expropriation the land and the amount of compensation to be paid clearly to the landholder or user in written considering the data it gets from the rural land administration and use office.
4. If the landholder or user is agrieved by the amount of compensation, he has the right to submit his petition to compensation grievance enquiry committee.

5. የካሣ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን መሬቱን ከለቀቀ በኋላ ውሳኔ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ በአቅርቢያው ለሚገኘው "ከፍተኛ ፍርድ ቤት" ይግባኝ የማለት መብት አለው። ይህ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ወገን ያለ እንደሆነ ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል።

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ሥር በተደነገገው መሠረት የካሣ ቅሬታ አጣሪ ኮሚቴ ያልተቋቋመባቸው ሥፍራዎች ሲኖሩ በካሣ መጠን ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን አቤቱታውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ በአቅራቢያው ለሚገኘው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ይኖረዋል።

7. ለሕዝብ አገልግሎት ከሚለቀቅ የገጠር መሬት ይዞታ ጋር በተያያዘ ካሳ የሚተመንበትና ለተነሽዎች የሚከፈልበት ስሌት ቀመር በደንብ ይወሰናል፤

8. ካሳ ከፋዩ መንግሥት፣ የግል ድርጅት፣ ኅብረተሰቡ ወይም ሌላ አካል ቢሆንም የካሳ መጠኑ ማስያ ቀመር አንድ አይነት ይሆናል።

9. በዚህ አዋጅ መሠረት በልማት ምክንያት ከመሬታቸው የሚፈናቀሉ ባለ ይዞታዎች ፍላጎታቸው እየታየ በሚነደፉ የመልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክቶች እንዲታቀፉ ይደረጋል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

5. Any party, who disagrees with the decision on the compensation grievance inquiry committee, has the right to appeal to the nearby "high court" after surrendering the land within 30 days since the decision is given. If there is also any party who thinks fundamental error of law is commited on the decision passed by this court, he shall have the right to submit his petition to the Cassasion Division of the Regional Supreme Court.

6. In areas where compensation appeal inquiry committee is not established according to the provision sub-article (5) of this Article, any party disagreed with the amount of compensation shall have the right to submit his petition, preparing in written form, to the nearby high court.

7. Compensation valuing and paying formula for the displaceds will be determined by a regulation concerning with the rural land dispossessed for public service.

8. In valuing amount of compensation, the same formula shall be applied notwithstanding the compensation payer is government, private organization, the society or another body.

9. The landholders displaced from their land for development purpose, in accordance with this proclamation, will be embraced by the will be designed re-settlement projects _ their needs being evaluated. Particulars will be determined by a regulation.

ክፍል ሶስት
ከገጠር መሬት አጠቃቀም ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ግዴታዎች

27. የገጠር መሬት ተጠቃሚ ግዴታዎች

1. ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ. በይዞታው ስር ያለውን ወይም በኪራይ ያገኘውን መሬት የመንከባከብና አካባቢውን የመጠበቅ፤

ለ. በመሬቱ ዙሪያ አስቀድመው የበቀሉ ነባር እፅዋት ቢኖሩ ዝርያቸው እንዳይጠፋ እነዚህኑ የመንከባከብ፤

ሐ. የራሱንም ሆነ የአጎራባች ባለይዞታዎችን ማሳ በማይጎዳ ሁኔታ በመሬቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሌላቸው ይልቁንም የአፈር ለምነቱን የሚያሻሽሉና ለአካባቢ ደህንነት ተስማሚ የሆኑ ዛፎችን የመትከልና በተገቢው ሁኔታ ተንከባክቦ የማሳደግ፤

መ. የመሬት ተዳፋትነታቸው ከ31 በመቶ እስከ 60 በመቶ የሆኑ መሬቶችን ለዓመታዊ ሰብሎች ልማት ለማዋል ይቻል ዘንድ እንደአስፈላጊነቱ ተስማሚ የሆኑ የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን የማከናወን፤

PART THREE
Obligations Related with Rural Land Use

27. Oblighations of Rural Land User

1. Any rural land user, according to this proclamation, has the following particular obligations:

A. Caring the land under his holding or he acquired through rent and protecting the environment;

B. Caring plants if there are grown round the land in advance in order not their species to be disappeared;

C. Planting trees in a way that does not harm his farm as well as his neighbourings that have no negative consequences on the land instead which improve the fertility of the land and suitable for the environment and treating them;

D. Carrying out, as its necessity, conducive soil conservation activities in order to use for perenial crops on lands where their slope is from 31 to 60 percents;

ሠ. ተገቢ ባልሆነ የአስተራረስ ዘይኤና ባልተመከረባቸው ዛፎች ተከላ ሳቢያ የውሃ ምንጮች እንዳይደርቁ የጥንቃቄ እርምጃዎችን የመውሰድ፤

E. Taking precuationary measures in order not water sources be dried due to inappropriate ploughing system and planting unrecommended plants;

ረ. የወል መሬት ይዞታዎችን ያለመዳፈር፣ በወሰን የተከለሉ ሌሎች መሬቶችን ድንበር ያለመጋፋትና ተለይተው የሚታወቁ የሕዝብ መንገዶችን ያለመዝጋት፤

F. Not trespassing communal lands; not violating delimitation of lands and not closing public roads thereto;

ሰ. ይዞታውን በመሬት አጠቃቀም ዕቅዱ መሠረት ይጠቀምበት ዘንድ አግባብ ባለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት አማካኝነት በጽሑፍ መመሪያ ሲሰጠዉ ይህንኑ አክብሮ የመፈጸም፤

G. Using the land based on the land use plan when ordered, in written, to do so by the pertinent land administration and use office.

ሸ. በመሬቱ አካባቢ የሚገኙ የዱር እንስሳትና አእዋፍ እንዳይታወኩ ወይም እንዳይጎዱ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ የመውሰድ፤

H. Taking appropriate care measures of wild animals and birds found around the land in order not to be disturbed or harmed;

ቀ. መሬቱ እንዲለካ ወይም የቅየሳ ሥራ እንዲከናወንበት አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ለዚሁ አድራጎት የመተባበር፤

I. Collaborating for this when asked by the pertinent body when his land to be measured or surveying work is carried out;

በ. የመሬቱ ባለይዞታ ራሱ ከሆነ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር በሚሰጥበት ጊዜ ይህንኑ ተከታትሎ የመውሰድ፣

J. Taking landholding certificate, following up, when he is a landholder at the time of distributing holding certificate.

ተ. የመሬት ይዞታ መብቱን በማናቸውም ምክንያት በሚያጣበት ጊዜ ለዚሁ የተሰጠውን የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አግባብ ላለው አካል ወዲያውኑ የመመለስ።

K. Returning the given land holding certificate immediately to the pertinent body when he is deprived of his holding right in any reason.

ቸ. እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ግዴታዎች፡፡

2. የገጠር መሬት ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም የግል ባለሃብት ወይም የኢንቨስትመንት ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ስር ከሰፈሩት አጠቃላይ ግዴታዎች በተጨማሪ ለተፈቀደለት የመሬት ይዞታ ተገቢውን የአጠቃቀም እቅድ በማዘጋጀት ሥልጣኑ ለሆነው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካል አቅርቦ የማስጸደቅና በዚሁ እቅድ መሠረት መሬቱን በጥቅም ላይ የማዋል ግዴታ አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ተዘጋጅቶ የሚቀርበው የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የኅብረተሰቡን ጤንነት፣ የአካባቢውን ደህንነትና የራሱን የመሬቱን ለምነት አጠባበቅ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፤

4. ተዳፋትነታቸው ከ8-30 በመቶ በሆነ የገጠር መሬቶች አካባቢ የተጠቃሚዎች የመሬት አያያዝ የአፈር ክለትን የሚቀንስ እና በእርጥበት-አጠር አካባቢዎች ውኃን የመያዝ ስልትን የተከተለ መሆን አለበት፤

5. ተጠቃሚዎች ተዳፋትነታቸው ከ31-60 በመቶ የሆኑ የገጠር መሬቶችን ለዓመታዊ ሰብሎች ልማት ማዋል የሚችሉት አግባብነት ባላቸው የአፈርና ውሃ እቀባ ቴክኖሎጂዎች በመደገፍ ብቻ ይሆናል፤

L. Other obligations similar to these.

2. Any private investor or investment institution being the rural land user, besides the general obligations provided under sub-article /1/ of this Article, shall have the obligation to prepare and submit appropriate use plan of the land he has been permitted presenting to the authorized body_the rural land administration and use body to get approved and use the land based on this plan.

3. The land use plan presented, being prepared, based on sub-article (2) of this Article, shall consider healthy of the society, wellbeing of the environment and fertility protection of the land.

4. The users land treatment in areas of rural land where their slope is from 8-30 percent shall reduce soil erosion, and follow a system of holding water in moisture lacked areas.

5. The users shall use the rural lands whose slope is from 31-60 percent for perenial crops development only when supported with appropriate soil and water conservation technologies.

6. ተጠቃሚዎች ተዳፋትነታቸው ከ60 በመቶ በላይ የሆኑ የገጠር መሬቶችን ከእርሻና ከልቅ ግጦሽ አገልግሎት ነጻ በማድረግ ለዛፍ፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለእንስሳት መኖ ልማትና እንደ ሁኔታው ለቱሪስት መስብነት ብቻ ማዋል ይኖርባቸዋል፤

6. The users shall use the rural lands having slopes above 60 percent for only, making free from ploughing and grazing, trees, permanent plants, and animals feed development and as its condition for tourist attraction.

7. የመሬት ተጠቃሚዎች በማናቸውም ዓይነት ተዳፋትነት የሚገኝንና ክፉኛ የተጎዳ የገጠር መሬት ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነጻ በማድረግ እንዲያገግምና ይኸው ሲረጋገጥ ብቻ በተለይ በሚወጣለት የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ላይ ተመስርቶ ጥቅም እንዲሰጥ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

7. The land users should make any kind of slope and heavily degraded rural land free from human and animal connection and let it to recover. When only this is ensured, they should use based on the land use plan prepared specifically for this.

8. የአካባቢው ማኅበረሰብ በጋራ ትብብር እንደ ፊዚካላዊና ስነ-ሕይወታዊ ያሉ ሥራዎችን በማከናወን ቦረቦራማ የሆኑና ክፉኛ የተጎዱ የገጠር መሬቶች መልሰው እንዲያገግሙና በጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ በተለይም ኮረብታማ በሆኑ አካባቢዎች በወል ወይም እንደ ሁኔታው በግል የተያዙ ሆነው በቦረቦር የተጎዱ የገጠር መሬቶች እንዲያገግሙና መልሰው እንዲለሙ መደረግ ይኖርባቸዋል፤

8. The local society in common collaboration should have a responsibility to carry out physical and biological works so that the eroded and heavily degraded rural lands be recovered and be used. Especially rural lands eroded being communally or conditionally privately owned hilly areas should be recovered and redeveloped.

9. የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች በተፈጥሮ የሚፈሱ ውኃዎች የታችኛውን ማሳ በማይጎዳ አኳኋን እንዲፋሰሱ የማድረግ ግዴታ አለባቸው::

9. Rural land users should have the obligation to divert the naturally flowing water in a way that does not damage the farm below them.

10. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ውኃ-አዘል የገጠር መሬቶች በየአካባቢው ማኅበረ-ሰብ ጥረትና ጉዳዩ በሚመለከተው አካል የሙያ ድጋፍ ተከልለው መጠበቅ ይኖርባቸዋል::

11. የውኃ ዳርቻዎችና ቦረቦር መሬቶች በጥናት እየተለዩ በተወሰነ እርቀት ከእርሻ እንቅስቃሴ ተከልለው መጠበቅ አለባቸው፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል::

12. በገጠር መሬት ላይ የመሰረተ-ልማት አውታሮችንና አዳዲስ የሠፈራ ፕሮግራሞችን የሚያስፈጽሙ አካላት የአካባቢ ደህንነትንና ተያይዘው ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን የመግቻ ስልቶችን ነድፈውና በዕቅዶቻቸው ውስጥ አካተው ገቢራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል::

13. ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ በክልሉ መንግሥት አማካኝነት የሚቀርቡ የተሻሻሉ ባህላዊና ሳይንሳዊ የመሬት አያያዝና አጠቃቀም ዘዴዎችን ተቀብሎ በሥራ ላይ የማዋልና የእርሻም ሆነ የግጦሽ መሬቶችን ምርታማነት የመጠበቅና የማሳደግ ግዴታ አለበት::

14. ማንኛዉም የገጠር መሬት ተጠቃሚ በዚህ አዋጅ መሠረት ከተፈቀደለት የይዞታና የመጠቀም መብት በላይ አስፋፍቶ እላፊ እንዳይዝ ተከልክሏል::

15. ማንኛዉም የገጠር መሬት ተጠቃሚ መሬቱን በሕግ ለተከለከለ ለማናቸውም ተግባር ሊያውለው አይችልም፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

10. Water holding rural lands found in the region shall be protected_being demarked by the effort of the local society and professional support from concerned body.

11. Coastal and gully lands being identified through research shall be protected in some distance from farming. Details will be determined by a regulation.

12. Bodies tasked with the implementation of infrastructure network and new settlement programs should design and implement reversing methods of problems caused in environmental wellbeing and related problems.

13. Any rural land user shall have the obligation to accept and implement improved traditional and scientific land holding and use methods presented by the regional government, and keeping as well as improving the productivity of farming and grazing lands.

14. Any rural land user is prohibited in order not to hold expanding beyond the permitted holding and using right in this proclamation.

15. Any rural land user may not use the land for any legally prohibited activity. Details will be determined by a regulation.

16. ማንኛዉም የገጠር መሬት ተጠቃሚ ማሳዉን አደገኛ ከሆኑ መጤና ተስፋፊ አረሞች መከላከልና መጠበቅ አለበት፡፡

16. Any rural land user shall prevent and protect his farm from dangerous foreign and spreading weeds.

28. ግዴታን አለመወጣት ስለሚያስከትለው ኃላፊነት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 ስር የተመለከተውን ወይም ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ወደፊት በሚወጡት ደንቦችና መመሪያወች ውስጥ የሚደነገጉትን የትኛዎቹንም ግዴታዎች ያልተወጣ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ በቅድሚያ እንደ ሁኔታው የቃል ወይም የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡
2. ባለይዞታው ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ ስር በተደነገገው መሠረት የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ተቀብሎ ስህተቱን ሊያርም ያልቻለ ወይም ለማረም ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ እንደሆነ ከዚህ በታች በተመለከተው ቅደም ተከተል መሠረት አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡-

ሀ. የራሱ በሆነ ድክመት መሬቱን ካለመንከባከቡ የተነሳ በመሬቱ ላይ ጉዳት ደርሶ ከተገኘ የመጠቀም መብቱን ለተወሰነ ጊዜ መሬቱን የመንከባከብ ኃላፊነት ለሚወስድ ለሌላ ሰው በኪራይ እንዲያስተላልፍ ሊወሰንበት ይችላል፤

ለ. ከዚህ በላይ የተመለከተው እርምጃ ተፈጻሚ ከሆነ በኋላ ጥፋቱን በተመሳሳይ ሁኔታ የደገመ እንደሆነ በመሬቱ የመጠቀም መብቱን ለተወሰነ ጊዜ ከማገድ ጀምሮ ላለማው ሀብት ብቻ ካሳ ተከፍሎት መሬቱን ከናካቴው እንዲለቅ እስከ ማስገደድ የሚደርስ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡፡

28. Liability of Non-Performance of Obligation

1. Any rural landholder that fails to carryout obligations provided under Article 27 of this proclamation and any other obligations that will be provided in a regulation and directives to implement this proclamation in the future_ as the case may be, he shall be given oral or written warning.

2. If the landholder is unable or is not unwilling to rectify his wrongs accepting the warning given for him in accordance with the provision under sub-article /1/ of this Article, the following administrative measure may be taken against him respectively:

A. If the land is damaged due to his failure to treat it, it may be decided to transfer the using right for specific time to another person who will take the protection responsibility through rent;

B. If he repeats the mistake after the above indicated measure is taken, a measure ranging from prohibiting his using right for specific time upto making to dispossessing the land forall _by paying compensation only for the property he developed on the land will be taken.

3. ከዚህ በላይ የሰፈሩት ድንጋጌዎች ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሬታቸውን ለመንከባከብ በተሳናቸው ዜጎች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

3. The provisions stipulated above here in above shall not be applicable on citizens who are unable to treat their land due to a reason beyond their capacity.

4. የወል መሬት ተጠቃሚ የሆነ ማንኛውም ሰው መሬቱን ለመንከባከብ ከሌሎች አቻ ተጠቃሚዎች ጋር አልተባበርም ያለ እንደሆነ ሕግ ባለማክበር ምክንያት እንደ ቅደም ተከተሉ የቃል ወይም የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ወይም እንዲደርሰው ይደረጋል፣

4. Any person being a communal land user will be given oral or written warning respectively for a reason of disrespecting law if he refuses collaboration with others to care the land.

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ስር የተደነገገው ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ ጥፋቱን በተመሳሳይ ሁኔታ ከደገመ የወል መሬቱን ከናካቴው እንዳይጠቀም ለተወሰነ ጊዜ ከማገድ ጀምሮ ለዘለቄታው እስከ መከልከል የሚደርስ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፤

5. If he repeats the mistake after a warning provided under sub-article (4) of this Article is given, an administrative measure ranging from depriving him from using the communal land for a specific time upto permanent deprivation will be taken against him.

6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ “27” ስር የሰፈሩትን ማናቸውንም ግዴታዎች ያላከበረ ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ ከወንጀል ተጠያቂነት በተጨማሪ ላደረሰው ጉዳት አግባብ ባላቸው የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ካሣ እንዲከፍል ሊወሰንበት ይችላል፤

6. Any rural land user who does not respect any of the obligations provided under Article “27” of this proclamation, in addition to criminal responsibility, he may be adjudged to pay compensation based on pertinent provisions of the civil code.

7. በዚህ አዋጅ መሠረት የገጠር መሬት ባለይዞታ ወይም ተጠቃሚ የሆኑ መንግሥታዊ የሆኑ መሥሪያ ቤቶች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማትና የብዙኃን ማኅበራት ከዚህ በላይ በአንቀጽ 28 ስር የሰፈሩትን ግዴታዎች ያልተወጡ እንደሆነ አግባብ ባላቸው የወንጀል እና የፍታብሔር ሕግጋት ድንጋጌዎች መሠረት በተመሳሳይ ተጠያቂዎች ይሆናሉ።

7. If governmental offices, non-governmental organizations, religious institutions and mass associations being the rural landholder or user in accordance with this proclamation fail to carryout obligations put under Article 28 above, shall be similarly responsible by provisions of pertinent criminal and civil code.

ክፍል አራት
ስለመሬት አጠቃቀም ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበሩ

29. መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ስለማዘጋጀት

1. ቢሮው አገር አቀፉን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መነሻ በማድረግ ወይም ከራሱ ነባራዊ ሁኔታዎች በመነሳት በክልሉ ውስጥ የሚተገበር መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡ በክልል ደረጃ የሚዘጋጀው መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መስፈርቱ
   ከ 1፡250,000 ያነሰ መሆን አይኖርበትም፡፡
2. የእያንዳንዱ ዞን ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ የክልሉን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት በማድረግ በዞኑ ነባራዊ ሁኔታ የሚተገበር የራሱን መሪ የመሬት አጠቃቀም እቅድ ያዘጋጃል፡፡ የዞኑ መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መስፈርት ከ 1፡100,000 ማነስ የለበትም፡፡

3. የእያንዳንዱ ወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት በውስጡ የታቀፈበትን ዞን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት በማድረግ እንደ ወረዳው ነባራዊ ሁኔታ የሚተገበር የራሱን መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡ የወረዳ መሪ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መስፈርት ከ1፡50,000 ማነስ የለበትም፡፡

PART FOUR
PREPARATION AND IMPLEMENTATION OF LAND USE PLAN

29. Preparing Land Use Masterplan

1. The bureau prepares a land use masterplan that will be implemented in the region on the basis of the national land use plan or on its own contextual situations. The scale of land use masterplan prepared by the region shall not be less than from 1:250,000.

2. Every zonal rural land administration and use department prepares its own land use masterplan on the basis of the regional land use masterplan that will be implemented in the context of the zone. The scale of the land use masterplan of the zone should not be less than from 1:100,000.
3. Every wereda rural land administration and use office prepares its own land use masterplan that can be implemented in the context of the wereda on the basis of the land use plan of the zone which the wereda is embraced in. The scale of the wereda masterplan land use should not be less than from 1:50,000.

4. አካባቢያዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ቀበሌን ወይም ተፋሰስን መሠረት ያደረገና ነዋሪውን ሕብረተ-ሰብ ያሳተፈ ሆኖ አግባብ ባለው የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት የቴክኒክ ድጋፍ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን መስፈርቱ ከ 1፡10,000 ማነስ አይኖርበትም፡፡

4. Whereas the local land use plan should be on the basis of kebele or watershed and being participative of the resident society, it should be prepared by the pertinent wereda rural land administration and use office technical support. The scale should not be less than from 1:10,000.

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ ስር የተደነገገው ቢኖርም ከፊል አርብቶ-አደሩ ለግጦሽ በሚጠቀምባቸው አካባቢዎች የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መስፈርቱ 1፡20,000 ድረስ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

5. Notwithstanding the provision under sub-article /4/ of this Article, the land use plan scale in areas where the semi-pastoralist uses for grazing will be prepared upto 1:20,000.

6. ቀበሌን ወይም ተፋሰስን መሠረት ያደረገ አካባቢያዊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለማዘጋጀት እንደ ተገቢነቱ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የቴክኒክ ኮሚቴዎችንና አሳታፊ የገጠር ግምገማ ቡድኖችን ማደራጀት አስፈላጊ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

6. To prepare a local land use plan on the watershed of kebele or watershed, as its appropriateness, it will be necessary to organize technical committees and participative rural evaluation groups at the level of wereda and kebele. Details will be determined by a regulation.

7. የትኛውም የገጠር መሬት ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት እንዲውል ሲደረግ፡-

7. When any rural land is made to be used for a specific service:

ሀ. የተሻለ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ የሚሰጥ መሆኑ፤

A. being to give a better economical benefit;

ለ. በአካባቢ ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ አለመኖሩ ወይም ተጽእኖው አነስተኛ ሆኖ መገኘቱ፤

B. absence of consequential impacts on the environment or being insignificant;

ሐ. አገልግሎቱ በተጠቃሚዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆኑ እየተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል፡፡

C. acceptance of the service by the users_ should be ensured.

30. የመሬት አጠቃቀም እቅዶችን ወቅታዊ ስለማድረግ

1. በክልል፣ በዞንም ሆነ በወረዳ ደረጃ የሚዘጋጁ መሪ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅዶች እንደተገቢነቱ አገር-አቀፉን ዕቅድ ወይም የየአስተዳደር እርከኑን ዕቅዶች ታሳቢ በማድረግ ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚሆን ጊዜ ውስጥ ወቅታዊ መደረግ ይኖርባቸዋል።
2. በአካባቢ ደረጃ የሚዘጋጅ አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ እንደአስፈላጊነቱ የሚከለስበትና ወቅታዊ የሚደረግበት ጊዜ ገደብ በደንብ ይወሰናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ ስር የተደነገገው ቢኖርም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ዉኃ-አዘል መሬቶች፣ እንዲሁም ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች እና የመሳሰሉት ስፍራዎች ባሉበት ሁኔታ በአግባቡ ተጠብቀው መያዝና መልማት ይኖርባቸዋል።

31. በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ውስጥ የመሬት አሰጣጥና አጠቃቀምን ስለመወሰን

1. በክልሉ በሚገኙ በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ የቀበሌ ማዕከላት እንዲኖሩ ይደረጋል። እነዚህ ማዕከላት የሚተዳደሩት በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል።

30. Updating Land Use Plans

1. The rural land use masterplans prepared at regional, zonal or wereda levels should be updated within 10 to 15 years considering, as its appropriateness, the national or administrational level plans.
2. As its necessity, the revising and updating limit of the participative rural land use plan prepared at local level will be determined by a regulation.
3. Notwithstanding the provisions under sub-articles /1/ and /2/ of this Article, in any condition, water holding lands as well as natural, traditional and religious heritages and soforth places should be properly preserved and developed.

31. Determining Land Provision and Use in Rural Kebele Centers

1. It will be made kebele centers are there in all rural kebeles in the region. These centers will be administerd by this proclamation and regulations and directives to be issued to implement this proclamation.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተደነገገዉ ቢኖርም ጉዳዩ የሚመለከተው የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት እንደአስፈላጊነቱ በጥናት ላይ ተመሥርቶ በአንድ ቀበሌ ዉስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ማዕከላት እንዲኖሩ ሊወስን ይችላል፡፡
3. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የተመሠረቱ የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ይቀየሩ ዘንድ በሕዝቡ በኩል ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ የሚመለከተው ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት በጥናት ላይ ተመሥርቶ በሚሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት ቅያሬው ሊፈቀድ ይችላል::
4. በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ውስጥ የሚተገበረው የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ አሰጣጥ ስርዓትና ግንባታው የሚያሟላቸው ስታንዳርዶች በደንብ ይወሰናሉ፡፡
5. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /4/ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነና በቀበሌው ውስጥ ቢያንስ ለተከታታይ ሁለት ዓመታት ነዋሪ ሆኖ በግብርና፣ በንግድ ወይም በሌሎች በማናቸውም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚሠራ ማንኛውም ሰው በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ውስጥ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ ያገኛል፡፡

2. Notwithstanding the provision under sub-article /1/ of this Article, the concerned wereda administration council, traced with a study as its necessity, may decide more than one kebele centers in a kebele be there.
3. If a request is presented by the people so as to be the rural kebele centers changed _established before the effective date of this proclamation, the change may be made based on the decision made by the concerned wereda administration council on basis of study.
4. The system of providing land and standards of building for house that will be implemented in rural kebele centers are determined by a regulation.
5. Without prejudice to the general provision under sub-article /4/ above, any person whose age is 18 years and above that has been residing in the kebele for atleast two consequetive years who is engaged in agriculture, trading or works in any other governmental and non-governmental organizations_ gets a parcel of land for building a house in the rural kebele centers.

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) ስር የተደነገገው ቢኖርም ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አቅመ ደካሞች፣ ሴቶችና አረጋውያን እንደ ቅደም ተከተላቸው በማዕከላቱ ውስጥ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ በቅድሚያ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል።

7. በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ውስጥ የተገነቡ መኖሪያ ቤቶች ቢሮው በዚህ አዋጅ መሠረት ለገጠር ቤቶች አሠራር በደንብ የሚደነግጋቸውን የዲዛይንና የግንባታ ጥራት መስፈርቶች አሟልተው ስለመገኘታቸው አግባብ ባለው የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ካልተረጋገጠ በስተቀር ሊሸጡ፣ የዕዳ ዋስትና ሆነው ሊያዙም ሆነ በማናቸውም መንገድ ለሶስተኛ ወገን ሊተላለፉ አይችሉም።

8. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በገጠር ቀበሌ ማዕከላት ውስጥ የተገነቡና በፕላኑ ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች የማያሟሉ ቤቶች ጉዳይ በደንብ ይወሰናል።

32. ወቅታዊ የመሬት አጠቃቀምን መቀየር የተከለከለ ስለመሆኑ

1. በጥናት ላይ ተመስርቶ ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም የገጠር መሬት ይዞታ ላይ ገቢራዊ በመደረግ ላይ ያለ ወቅታዊ የአጠቃቀም ዕቅድ በዘፈቀደ አይቀየርም። ሆኖም ይህ ድንጋጌ ተዳፋትነታቸዉ ከ50 ፐርሰንት በላይ የሆኑ የመሬት ይዞታዎች ወደ ቋሚ ተክሎች ማልማያነት ከማሸጋገር የሚከለክል አይሆንም።

6. Notwithstanding the provision under sub-article (5) of this Article, children who lost their parents, disables, weaklings, women and ageds respectively shall have priority right to get land for building a house in the rural kebele centers.

7. Houses built in the rural kebele centers can not be sold_ being mortgaged as well as transferred to a third party in any means unless the requirements of design and building quality those are provided by the bureau that will be issued to implement this proclamation are acertained by the pertinent wereda rural land administration and use office.

8. The issue of houses built in the rural kebele centers before the effective date of this proclamation and which do not meet the requirements indicated in the plan shall be determined by a regulation.

32. Prohibition of Changing the Updated Land Use

1. Unless it is based on a study, the updated use plan being functional on any rural land is not changed haphazardly. However, this provision does not prohibit transferring the land holdings whose slope is above 50 percent to permanent plants development.

2. የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ተብለው ከተመረጡት ስፍራዎች ውጭ በእርሻ፣ በግጦሽ፣ በወልና በደን መሬቶች ላይ ማናቸውንም አይነት አዲስ ግንባታ ማካሄድ የተከለከለ ነው::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ስር የተመለከተው የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ተዘጋጅቶ ባልተሰጠበት አካባቢ አርሶ አደሩ በመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ ላይ ባስመዘገበው ይዞታ ውስጥ ለራሱና ለአካለ-መጠን ለደረሱ ልጆቹ በሚበቃ መጠን በቤተ-ሰቡ አባላት ስም ባስመዘገበው ይዞታ ውስጥ የመኖሪያ ቤት ከመገንባት አይታገድም::

2. Except the places designated as rural kebele centers, it is prohibited to carryout any kind of new building on farm, grazing, communal and forest lands.
3. In areas where a land use plan, indicated in the provision under sub-article /1/ of this Article is not prepared and handed, a farmer is not prohibited from building a house for himself and to his children who have attained majority on his holding that he has got registered in the name of his family members on the landholding certificate.

ክፍል አምስት
የገጠር መሬትን ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ስለ መስጠት

PART FIVE
MEASURING, REGISTERING OF RURAL LAND AND GIVING LANDHOLDING CERTIFICATE

33. ይዞታን ስለመለካት

33. Measuring Landholding

1. ለተጠቃሚዎች በይዞታነት የተሰጠ በአንድ አካባቢ ማኅበረ-ሰብ በወል የተያዘ ወይም ለደን ልማት ወይም ለሌሎች መሰል ተግባራት የተከለለ የትኛውም የገጠር መሬት በባህላዊ መንገድ ወይም በዘመናዊ መሳሪያ ተለክቶ ካርታ ይዘጋጅለታል፡፡

1. A map is prepared for any rural land given to users in holding, held communally by a local community or for forestery development or other similar functions by measuring in traditional method or by modern instrument.

2. የግል፣ የወልና የመንግሥት ይዞታዎች እንደ ሁኔታው በተለያዩ የቅየሳ መሳሪያዎች እየተለኩ ድንበሮቻቸውን የሚያሳይ ምልክት ይደረግባቸዋል::

2. A mark indicating their boundaries for private, communal and government holdings being measured with different surveying materials are made as the case may be.

3. በዚህ አይነት የተለካው መሬት ባለይዞታዎች የይዞታቸውን መጠንና አዋሳኝ ድንበሮች የሚያሳይ ካርታ ተዘጋጅቶ ይህንኑ ከሚያረጋግጥ ደብተር ጋር ይሰጣቸዋል፡፡
4. የትኛውም መሬት በሚለካበት ጊዜ በተቻለ መጠን የመሬቱ አዋሳኝ ባለይዞታዎች ወይም ተወካዮቻቸው በስፍራው ተገኝተው ድንበሮቻቸውን እንዲያሳዩ ጥሪ ይደረግላቸዋል፡፡ የመሬቱ ቅየሳ የሚካሄደውም የባለይዞታዎችን ማሳዎች መነሻ በማድረግ ይሆናል፡፡
5. በመሬቱ አለካክና በድንበሩ አከላለል ረገድ ቅሬታ የተሰማው ማንኛውም ባለይዞታ ቅር የተሰኘበትን ምክንያት በዝርዝር በመግለጽ ልኬታው በተጠናቀቀ 30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩ እንደገና ይታይለት ዘንድ በየደረጃው ለሚገኘው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካል የማቅረብ መብት አለው፡፡
6. የትኛውም መሬት ከተለካ በኋላ መጠኑ በተለያዩ ምክንያቶች ተለውጦ የተገኘ እንደሆነ እንደገና ተለክቶ አዲስ ካርታ ይዘጋጅለታል፡፡
7. ፈቃድ ያላቸውና በግል ሥራ የተሰማሩ የቅየሳ ድርጅቶች በመሬት ቅየሳ ሥራው ላይ እንዲሳተፉ ሊደረግ ይችላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

34. ስለመሬት ምዝገባና የመረጃ አያያዝ

1. ይህንን አዋጅ መሠረት በማድረግ አግባብ ባለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አካል ኃላፊነት የተለካ ማናቸውም የገጠር መሬት ይዞታ ለዚሁ ዓላማ በተቋቋመው የመሬት መዝገብ ውስጥ ይመዘገባል፤

3. A map that indicates the amount and boundaries of the land of landholders is prepared in this way and given for them with landholding certificate.
4. Adjecent landholders or representatives will be notified, as much as possible, to show their boundaries being present at the place when any land is measured. The land survey is carried out benching on the landholders' farm.
5. Any landholder being aggrvied on the measurement and demarcation of the land has the right to submit his claim_ listing clearly so as to be seen again to any level of rural land administration and use body within 30 days of completion of the measurement.
6. If the size of any land is found to be changed in different reasons after it is measured, a new map is prepared for it after being re-measured.
7. Surveying organizations which are licensed and privately engaged in survey work may participate in the land surveying. Particulars shall be determined by a regulation.

34. Land Registration and Data Keeping

1. On the basis of this proclamation, any rural landholding measured by the responsibility of pertinent rural land administration and use body is registered in the land file which is established for this objective.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር በሰፈረው ድንጋጌ መሠረት የሚካሄደው የገጠር መሬት ምዝገባ የመሬቱን ባለይዞታ ሙሉ ስም፣ ይዞታው የተገኘበትን ሁኔታ፣ የመሬቱን አዋሳኞች፣ የለምነቱን ደረጃ፣ መሬቱ የሚውልበትን አገልግሎትና ባለይዞታው ያለበትን ግዴታዎች የሚገልጽ መረጃ አካቶ መያዝ ይኖርበታል።

2. The rural land registration carried out in accordance with sub-article (1) of this Article shall include the full name of the landholder, the condition of holding is aquired, boundaries of the land, fertility level of the land, service of the land and descriptions of obligations the landholder has.

3. ከመሬቱ ጋር ተያያዥነት ያለውን መብትና ግዴታ የሚመለከት ማናቸውም ጉዳይ መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ላለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ በስተቀር በሶስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብባቸው አይችልም።

3. Any right and obligation attached to the land may not be raised as a defence against third parties unless it is registered by the wereda rural land administration and use office where the land is found.

4. መሬት-ነክ መረጃ በባሕረ-መዝገብም ሆነ ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀዉ የኤሌክትሮኒክስ ቅጅ ላይ መመዝገቡ በሕግ ፊት እኩል ተቀባይነት ይኖረዋል።

4. Registration of land-related data either in a master document or in electronical copy prepared for this objective shall have equal value before the law.

5. በሀሰተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ማናቸውም ምዝገባ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፤

5. Any registration carried out based on false data shall not have legal effect.

6. በመዝጋቢው ስህተት ምክንያት በማንኛውም ሰው ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ስህተቱን የፈጠረው የመንግሥት አካል በፍታብሔር እና በወንጀል ኃላፊነት ተጠያቂ ይሆናል።

6. When harm is occurred on any person due to the fault of the registrar, the government body that committed the fault shall be accountable by both civil and criminal responsibility.

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /6/ ድንጋጌ አተገባበር ሳቢያ ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግሥት አካል በስህተቱ ለተጎዳው ወገን ካሳ እስከ መክፈል የደረሰ እንደሆነ ይህንኑ እንዲመልስለት ስህተቱን የፈጠረውንና ለባለዕዳነት የዳረገውን መዝጋቢ ሠራተኛ በተራው የመጠየቅ መብት ይኖረዋል። ሆኖም መዝጋቢው ሠራተኛ በኃላፊነት የሚጠየቀው ስህተቱን የሰራው ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ነው።

8. አስመዝጋቢውም ቢሆን በምዝገባዉ ለተፈጠረው ስህተት የራሱ አስተዋፅኦ እንደነበረው የተረጋገጠ ከሆነ በፍታብሔርና ተገቢ ሆኖ ሲገኝም በወንጀል ሕግጋት ተጠያቂ ይሆናል።

7. Where the concerned government body approaches upto paying compensation to the victim due to the fault upon the implementation of sub-article /6/ of this article, it shall have the right to claim from the registrar who committed the fault to re-verse the payment. However, the registrar will be liable when he commits the fault intentionally or negligently.

8. The person who applied for registration as well becomes subject to civil and in appropriate cases to criminal responsibility if it is proved that he had contribution for the fault committed.

35. ስለ ገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር

1. የገጠር መሬት በይዞታ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የመሬቱ ዝርዝር የተመዘገበበት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ ተዘጋጅቶና ፎቶግራፍ ተለጥፎበት አግባብ ባለው የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት በኩል ይሰጠዋል።

2. የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የባለይዞታው በሕግ የተጠበቀ መብት ማስረጃ ነው። የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እያለ ዳኞች ሌሎችን የሰነድም ሆነ የሰው ማስረጃዎችን ቅድሚያ ሰጥተው ሊቀበሉና ሊመለከቱ አይችሉም።

35. Rural Landholding Certificate

1. A landholding certificate containing the land list, being prepared in his name and photgraph is attached will be given to any rural landholder through the pertinent wereda rural land administration and use office.

2. The landholding certificate is an evidence of the legally protected rights of the landholder. Judges may not consider any documentary evidence or any witness before consulting the landholding certificate while there is a certificate.

3. መሬቱ በባልና ሚስት ወይም በሌሎች ሰዎች በጋራ የተያዘ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ የሚዘጋጀው በሁሉም ወገኖች ስም ይሆናል።

4. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአንደኛው ስም ብቻ ተዘጋጅቶ ከተሰጠ በኋላ ጋብቻ የተፈፀመ እንደሆነ ተጋቢዎች መሬቱን የጋራ ይዞታ ለማድረግ ሊስማሙ ይችላሉ። ባልና ሚስት የግል የነበረውን መሬት በስምምነት የጋራ በሚያደርጉበት ጊዜ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በሁለቱ ስም ይዘጋጃል።

5. ይህንኑ የሚቃረን ጠንካራ የጽሑፍ ማስረጃ እና ይበልጥ የሚያሳምን ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስሙ ተዘጋጅቶ የተሰጠው ማንኛውም ሰው የመሬቱ ሕጋዊ ባለይዞታ እንደሆነ ይቆጠራል።

6. የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የባለይዞታውን በሕግ የተደነገጉ ዋና ዋና መብቶችና ግዴታዎች ማመላከት አለበት።

7. በሕግ ከተወሰነው የአንድ ማሳ ዝቅተኛ መጠን በታች የሆነ የትኛውም የገጠር መሬት በይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ውስጥ ለብቻ አይመዘገብም። ሆኖም ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የነበሩ አነስተኛ ይዞታዎችን በሚመለከት ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

3. The land certificate shall include the names of all parties if the land is held by spouses or by other persons in common.

4. When marriage is concluded after the landholding certificate is given in the name of one spouse, both spouses may agree to hold the land in common. Where the spouses make the land common holding, the certificate shall include the name of both spouses.

5. The person who is guaranteed with landholding certificate in his name shall, unless a strong contrary written evidence or better persuasive reason is submitted, be considered as legal holder of the land.

6. The landholding certificate shall indicate the main rights and obligations of the landholder.

7. Any rural land which is less than the minimum limit of holding shall not be registered alone in the landholding certificate. However, details concerning the minimum holdings available before the effective date of this proclamation will be determined in a regulation.

8. በዚህ አዋጅ መሠረት የገጠር መሬትን ከሚያስተዳድረው አካል ተፈላጊው የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ሳይሰጠው በክልሉ ውስጥ በገጠር መሬት ሲጠቀም የተገኘ ማንኛውም ሰው ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ መሬቱን እስከ ማስለቀቅ ለመድረስ የሚችል እርምጃ ይወሰድበታል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

8. Any person to be found using the rural land in the region without getting the necessary landholding certificate from the rural land administrative body in accordance with this proclamation_ a measure starting from oral warning to displacing him from the land shall be taken. Details will be determined by a regulation.

9. የወል መሬት ተጠቃሚዎች የሆኑ ባለይዞታዎች ይህንኑ የሚያመለክት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስማቸው ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል፤

9. Communal landholders will be issued landholding certificate containing their names.

10. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በማናቸውም መንገድ ቢሆን ያለፈቃድ በግለሰቦች ይዞታ ስር የወደቀ የወል መሬት ሁኔታ ተጣርቶ ወደ ነበረበት የወል ይዞታነት ይመለሳል። ያለ አግባብ ሲጠቀምበት የቆየ ሰው መኖሩ ከተደረሰበትም በፍትሐብሔርና በወንጀል ሕግጋት ይጠየቃል።

10. Without prejudice to the provision of sub-article (9) of this Article, a communal land being fallen under the individual's landholding without permission in any way is returned to the previous communal landholding being investigated. If it is found that an individual has been using the communal land, a person may be subjected to civil and criminal liability.

11. ተቋማትን በሚመለከት የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስማቸው ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል። የመሬት መጠኑና የአሰጣጥ ሁኔታው ዝርዝር በደንብ ይወሰናል።

11. A rural landholding certificate is given for institutions being prepared by their names. Details of the amount of land and giving condition shall be determined by a regulation.

36. ስለ መሬት ይዞታ ምዝገባ ስርዓት

36. Registration System of Landholding

1. በክልሉ ዉስጥ የሚደረግ የገጠር መሬት ይዞታን የማረጋገጡ ተግባር በአንድ አካባቢ ያሉ ማሳዎችን አስገዳጅ በሆነ አሠራር በመደዳ በመለካትና በመመዝገብ ይከናወናል።

1. The function of assuring the rural landholding in the region shall be accomplished by measuring and registering plot in an area through an obligatory way.

2. የምዝገባ ስርዓቱ እንደ ተገቢነቱ ይዞታን ወይም ማሳን መሠረት በማድረግ ይከናወናል፡፡

37. ይዞታን የማረጋገጥ ሂደት

1. የገጠር መሬት ይዞታን የማረጋገጥ ሂደት ጉዳዩ በሚመለከተው በቀበሌ ወይም ንዑስ ቀበሌ ውስጥ በሚኖረዉ ባለይዞታና አግባብ ባለው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አማካኝነት በሕዝብ በማስተቸት ይፈፀማል፡፡ ለዚሁ ዓላማ የተመደበው ባለሙያም የማስተቸቱን ተግባር ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡
2. በቀበሌም ሆነ በንዑስ ቀበሌ ደረጃ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አባል ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሰው የራሱ የሆነን ወይም የቅርብ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዱን ይዞታ በማጣራት ሥራ ላይ አይሳተፍም፡፡ ተሳትፎ ቢገኝ እንኳ ተጣርቶ የተገኘው ማናቸውም አይነት መረጃ ውድቅ መደረግ ይኖርበታል፡፡

38. የመሬት ይዞታውን በመመዝገብና በማረጋገጥ ሂደት የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የገጠር መሬት ይዞታን በመመዝገብ እና በማረጋገጡ ሂደት በባለይዞታዎች መካከል ክርክር የተነሣ እንደሆነ ባለጉዳዮቹ አግባብ ባለው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አቀራራቢነት

2. The registering system, as its appropriateness, shall be implemented on the basis of landholding or plot.

37. The Process of Assuring Landholding

1. The process of assuring the rural landholding is implemented between the pertinent landholder residing in the kebele or sub-kebele and a pertinent land administration and use committee by getting criticized to the people. The officer assigned for this purpose follows and supports the function of getting criticized.

2. Any person found to be serving as a committee member of rural land administration and use at kebele as well as sub-kebele level shall not participate in the implementation of checking the landholding of his close consanguineal or affinal filiation. If he is found to be participated, any kind of data found being checked shall be made invalid.

38. Determing Disputes Arised from the Process of Registering and Assuring Landholding

1. If dispute is arised between and among holders in the process of registering and assuring the rural land based on this proclamation, the parties are made to get agreed by the negotiator of the pertinent land

እንዲስማሙ ይደረጋል፤ በዚህ ያልተስማሙ እንደሆነ ኮሚቴው ከቀበሌው የመሬት ዘርፍ ባለሙያ በሚገኘው መረጃና አስተያየት ላይ ተንተርሶ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2. በዚህ የቀበሌው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን በየደረጃው ለሚገኘው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

3. በተቋሙ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ደግሞ ክሱን በ30 ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው የወረዳ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

4. ያልተቋጨ ክርክር ያለበት ማናቸውም ማሳ "በክርክር ላይ ያለ" ተብሎ በኮሚቴዉ ይያዛል፡፡

39. የሕፃናትን፣ የአካል-ጉዳተኞችን፣ የአቅመ-ደካሞችን፣ የሴቶችን፣ የአረጋውያንንና በአካባቢው ያልተገኙ ሌሎች ሰዎችን መብት ስለመጠበቅ

1. ሞግዚት ወይም ሕጋዊ ወኪል የሌላቸው ሕፃናት፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የአቅመ ደካሞች፣ የሴቶችና የአረጋውያን ይዞታ የሆነ መሬት በሚመዘገብበትና በሚረጋገጥበት ወቅት እነዚሁ ወገኖች በስፍራው ካለመገኘታቸው የተነሳ መብታቸው እንዳይጣስ ብርቱ ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡

administration and use committee. If they do not agree, the committee will give administrative decision based on the data and suggestion obtained from the kebele land officer.

2. The party who disagrees on the kebele dicision may submit his claim to the rural land administration and use office found at each level.

3. The party, who disagrees on the administrative decision of the institution, can apply a suit to a wereda court having jurisdiction within 30 days.

4. Any plot petition has unconcluded dispute is kept as "debate on progress" by the committee.

39. Protecting the Right of Children, Disables, Weaklings, Women, Ageds and Other Absent Persons

1. A high care must be taken when the holding of children's those who have no guardian or legal agent, disables', weaklings', women's and ageds' is get registered and assured in order not their right is violated due to the absence of these parties.

2. የገጠር መሬት ይዞታን በመመዝገብና በማረጋገጥ ሂደት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በአካባቢው ያልተገኙ ሰዎችን መብት የሚያስጠብቅ የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይደነገጋል።

40. የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ በያዘው መረጃ ላይ ተቃውሞ ስለማቅረብና ማሻሻያ ስለማድረግ

1. የትኛውም የገጠር መሬት ይዞታ በምዝገባ ሂደት ተረጋግጦ የተያዘ መረጃ የመጨረሻ ሆኖ ለዚሁ በተቋቋመው መዝገብ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ቅሬታ ያለው ወገን ቢኖር አቤቱታ የሚያቀርብበት ስነ-ስርዓትና የጊዜ ገደብ በደንብ ይወሰናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚወሰነው የጊዜ ገደብ ከ6 ወር ሊበልጥ አይችልም።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ስር የተደነገገው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ማንኛውም ባለይዞታ የተመዘገበውን መረጃ በሚመለከት የሚያቀርበው ተቃውሞ ተቀባይነት አይኖረውም። ሆኖም ከፍ ብሎ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቅሬታውን ሳያቀርብ የቀረው ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ገልፆ ስለዚሁ ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የፅሑፍ ማስረጃ ያቀረበ እንደሆነ ከዚህ በላይ የሰፈረው ድንጋጌ ዘግይቶም ቢሆን ከመስተናገድ ሊከለክለው አይችልም።

2. The working procedure that enables to keep the right of persons who were absent at the time of registration and acertainment due to force majeur will be designed. The detail will be provided in a regulation.

40. Submitting Objection and Making Amendment on the Data of Rural Landholding Assurance Document

1. If there will be an aggrieved party before the data of any rural landholding is entered in the document_established for this being cheked and as a final in the registration process; the procedure of a grievance submission and time limit will be determined by a regulation.
2. The time limit that will be determined in accordance with sub-article /1/ of this Article may not exceed from 6 months.
3. An objection submitted after the expiry of the time limit stated under sub-article /2/ of this Article regarding the registered data shall not be accepted. However, if he has not submitted his grievance within the time limit decided above due to force majeur and submits his reason to the authorized body for this, the provision above can not prohibit him from being treated lately.

41. ስለ ገጠር መሬት ይዞታና የማሳ መለያ ቁጥሮች አሰጣጥ

1. በክልሉ ውስጥ የገጠር መሬት ይዞታና የማሳ መለያ ቁጥሮች የሚሰጡት የክልሉን መንግሥት አስተዳደራዊ እርከኖች በመከተል ከላይ ወደ ታች ይሆናል።
2. እያንዳንዱ የገጠር መሬት ይዞታና ማሳ የራሱ የሆነ ልዩ ኮድ እየተሰጠው ይመዘገባል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

ክፍል ስድስት
ስለ ገጠር መሬት ምዝገባ መረጃ አያያዝ፣ አጠባበቅና ወቅታዊ አደራረግ

42. ስለ መሬት መረጃ አያያዝ፣ አጠባበቅና መረጃ የማግኘት መብት

1. የገጠር መሬት ምዝገባ መረጃ ባሕረ-መዝገብ በሁለት ቅጅ ተዘጋጅቶ አንደኛው ቅጂ በሚመለከተው ቀበሌ ጽህፈት ቤትና ሁለተኛው ቅጅ ደግሞ ቀበሌው በሚታቀፍበት ወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ይቀመጣሉ። በሁለቱ የባሕረ-መዝገብ ቅጂዎች መካከል ልዩነት ተፈጥሮ የተገኘ እንደሆነ መረጃዉ እንደገና እንዲጣራና እንዲስተካከል ይደረጋል።

41. Providing Identity Number of a Plot and Rural Landholding

1. The rural landholding and plot identity number in the region shall be given from top to bottom following the administrative level of the regional state.
2. Every rural landholding and plot is registered being given its own special code. Details will be determined by a regulation.

PART SIX
DATA KEEPING, PROTECTION AND UPDATING OF THE RURAL LAND REGISTRATION

42. Data Keeping, protection and Right of Accessing Information

1. The master-document of rural land registration data, being prepared by two copies, the first copy is kept in the pertinent kebele office and the other copy is in the wereda land administration and use office where the kebele is embraced. If there exists discrepancy between the two copies, the data shall be re-checked and corrected accordingly.

2. የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በሚታደስበት፣ በሚተካበት ወይም ሌሎች መሰል አገልግሎቶች በሚሰጡበት ጊዜ ተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ይፈጸማል።

3. ማናቸውም የምዝገባ ሰነዶችና ሌሎች መሬት ነክ መረጃዎች ለሕዝብ ክፍት የሚደረጉበት ሁኔታና እንዳስፈላጊነቱም የእነዚህኑ ሰነዶች ትክክለኛ ቅጂ ለማግኘት የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ መጠን በደንብ ይወሰናል።

43. የምዝገባ መረጃን ወቅታዊ ስለማድረግ

1. የባለ ይዞታው ወይም የማሳ ወይም የሁለቱም ለውጥ በሚያጋጥምበት ጊዜ የመሬት ምዝገባ ሰነዱም ወቅታዊ መደረግ ይኖርበታል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
2. የገጠር መሬት ምዝገባ መረጃን ወቅታዊ የማድረጉ ተግባር በቀበሌ እና በወረዳ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች አማካኝነት ይከናወናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በተሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን በጽሑፍ አዘጋጅቶ አግባብ ላለው የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ሊያቀርብና ሊያስመረምር ይችላል፤ ሆኖም በውሳኔው ያልተስማማ እንደሆነ ቀጥሎ እንደ አግባብነቱ ጉዳዩ ወደሚመለከተው ዞን ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ ወይም ወደ አቅራቢያው ወረዳ ፍርድ ቤት ከማቅረብ አይታገድም።

2. The necessary payment is effected when the rural landholding certificate is renewed; replaced or other similar services are rendered.

3. The condition of making every registration documents and other land-related data open to the people and, as its necessity, the service payment amount for getting the authenticated copies of these documents will be determined by a regulation.

43. Updating the Registration Data

1. The land registration document must be updated when there faces changes of the landholder or farm or both. The detail shall be determined by a regulation.
2. The function of updating the rural land registration data is carried out by the kebele and wereda land administration and use committees.
3. If there is a party disagreed by the decision given based on sub-article 2 of this Article, he can submit his written petition to the pertinent wereda rural land administration and use office and get checked. However, he is not prevented from submitting his appeal, as its appropriateness, to the next pertinent zone rural land administration and use department or the nearby wereda court if he does not agree with the decision.

4. የገጠር መሬት ምዝገባ መረጃን ለማሻሻል ወይም ወቅታዊ ለማድረግ ጥያቄ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብና የመሳሰሉት ዝርዝር ጉዳዮች በደንብ ይወሰናሉ።
5. የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ መዝጋቢው አካል የይዞታ ምዝገባ መረጃውን በተቻለ ፍጥነት የማስተካከል ኃላፊነት አለበት።
6. ከዚህ በላይ በሰፈሩት የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት ጉዳዩ በሚመለከተው ወገን በጊዜው ቀርቦ ወቅታዊ ያልተደረገ ማናቸውም የገጠር መሬት የምዝገባ መረጃ ለውጥ ወይም ማሻሻያ በሕግ ፊት ውጤት አይኖረውም።

44. በክልሉ መንግሥት የአስተዳደር እርከኖች መካከል ስለሚኖረው የመረጃ ልውውጥና የርስ በርስ ቅንጅት

1. በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የተያዘው የገጠር መሬት መረጃ-ቋት ከክልሉ የገጠር መሬት የመረጃ-ቋት ጋር የተጣጣመና የተቀናጀ መሆን ይኖርበታል።
2. እያንዳንዱ ዞን ወቅታዊ የገጠር መሬት መረጃዎችን በየጊዜው ወደ ክልሉ የመረጃ-ቋት ይልካል። የመረጃው አይነትና ይዘትም በክልሉ የመረጃ አስተዳደር ስርዓት ይወሰናል።

4. The request of time limit and similar particulars to ammend the rural land registration data or updating shall be determined by a regulation.
5. If the submitted request is accepted, the registrar body has a responsibility to correct the holding registration data as fast as possible.
6. Change of any rural land registration data or improvement which is not updated being presented to the pertinent body on the basis of the provisions stated above this Article will not have effect before the law.

44. Information Exchange and Reciprocal Intergration between Administrative Levels of the Regional Government

1. The rural land database held by the zone, wereda and kebele should be balanced and integrated with the regional rural land database.
2. Every zone, from time to time, sends the updated rural land data to the regional database. The type and content of data shall be determined by the regional data administration system.

45. ስለ ገጠር መሬት ካዳስተር ቅየሳ

1. የክልሉ የገጠር መሬት ካዳስተር በአገር-አቀፍ ደረጃ ከሚሠራባቸው የመሬት መቆጣጠሪያ ነጥቦች ጋር እንዲተሳሰር መደረግ አለበት፡፡
2. በክልሉ ውስጥ የሚከናወነው የገጠር መሬት ቅየሳ አገር-አቀፉን የኮኦርድኔት ስርዓት የሚጠቀም ሲሆን የቅየሳ ሥራውም የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ ባወጣው የዳተም ዝውውር መስፈርት ላይ ተመስርቶ ይከናወናል፡፡
3. በገጠር ካዳስተር ቅየሳ የመለኪያ አሀዶች በደንብ ይወሰናሉ፡፡
4. የገጠር መሬት ቅየሳ በምድርና በፎቶግራ-ሜትሪክ ቅይጥ ዘዴዎች ሊካሄድ ይችላል፣
5. በወረዳ ደረጃ የሚዘጋጀው መሠረታዊ ካርታ የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ በሚያወጣቸው መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ መካደፍ ይኖርበታል፡፡
6. የወረዳና የቀበሌ መሠረታዊ ካርታዎች የሚይዟቸው ዝርዝር መስፈርቶች እና የአሠራር ስርዓቶች በደንብ ይወሰናሉ፡፡

45. Cadaster Surveying of Rural Land

1. The regional rural land cadaster should integrate with the national land controlling points.
2. Whreas the rural land surveying implemented in the region uses the national coordinate system; the surveying work is accomplished based on the datum transfer criterion issued by the Ethiopian Map Work Agency.
3. The units of rural cadaster surveying measurement shall be determined by a regulation.
4. The rural land surveying will be carriedout by the combination of land and photogrammetric systems.
5. The fundamental map prepared at the wereda level should be designed on the basis of criteria issued by the Ethiopian Map Work Agency.
6. The particular criteria and working procedures of the wereda and kebele fundamental contents of maps shall be determined by a regulation.

ክፍል ሰባት
ስለ አዋጁ አስፈጻሚ አካላት

46. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ

1. ይህንን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በበላይነት የማስፈጸም ኃላፊነት የተሰጠዉ የክልሉ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ከዚህ በኋላ (ቢሮዉ) እየተባለ የሚጠራዉ አካል ነዉ፡፡

2. አስቀድሞ በተቋቋመበት የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ አስፈጻሚ አካላት መልሶ ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 230/2008 ዓ.ም አንቀጽ 20 እና በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው፡-

ሀ. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የገጠር ቀበሌ ማዕከላት ፕላን ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል ወይም ይኸው በተዋረድ አካላቱ አማካኝነት ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲዘጋጅ ወይም እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡

ለ. የተዋረድ አደረጃጀቶችን በማጠናከርና ተፈላጊውን የሙያም ሆነ የማቴሪያል ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ ይህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

PART SEVEN
EXECUTIVE BODIES OF THE PROCLAMATION

46. The Rural Land Administration and Use Bureau

1. The regional rural land administration and use bureau hereafter called “the bureau” is a supper organ responsible to make this proclamation and regulations and directives those will be issued based on the proclamation to be implemented.

2. Without prejudice to the power given by the regional state executive bodies revised establishment and powers and responsibilities determiniation proclamation No 230/2016 Article 20, and by other laws, the bureau:

A. Prepares and improves the plan of rural kebele centers found in the region or causes to be prepared and improved by qualified professionals under its down structure.

B. Makes to be functional this proclamation and regulations and directives issued following this proclamation by strengthening bottom organizations and making the necessary professional as well as material support.

47. የዞን ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ ሥልጣንና ተግባር

የዞን ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መምሪያ በተደራጀበት አካባቢ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የግል ባለሃብቶች በመሬት ላይ የልማት ሥራ ከመጀመራቸው በፊት የአጠቃቀም ዕቅዳቸውን እየገመገመ ያፀድቃል፤ የኢንቨስትመንት መሬት ሊዝ አሠራርና ተመኑን በየጊዜው እያጠና ለቢሮው አቅርቦ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አማካኝነት ያስወስናል፤ በሕግ ተለይቶ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከባለሃብቶች ጋር ውሎችን ይዋዋላል፤ እንደ ውሉ በማይፈጽሙት ላይ ደግሞ በሕግ አግባብ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፡፡

2. ከቢሮውና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሌሎች የየአስተዳደር እርከኑ አካላት ጋር በመተባበር ለሕዝብ ጥቅም ታልሞ በሚወሰድ እርምጃ ምክንያት ከመሬታቸው የሚፈናቀሉ ባለይዞታዎች በቅድሚያ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፈላቸውና አማራጭ የኑሮ መሠረት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

47. Powers and Functions of Zonal Rural Land Administration and Use Department

Zonal rural land administration and use department in its organizational area, according to this proclamation, has the following particular powers and functions:

1. Evaluates and approves the use plan before the private investors start development work on the land; makes to be determined the investment land lease procedure and its estimation by studying periodically and presenting to the bureau through the council of regional government; makes contracts with investors based on its power given specifically by law; takes and causes to be taken legal measures on those who do not implement accordingly the law.

2. Facilitates conditions, in collaboration with the bureau and other pertinent administrative level bodies, to be paid a commensurate compensation and to get an alternative livelihood for displaced landholders when their land is taken for public purpose.

3. በዘመናዊ መንገድ በሚለሙ ትላልቅ የመስኖ-ልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ የሚኖሩ ቀደምት ባለይዞታዎች በሕግ አግባብ የመሬት ሽግሽግ እየተካሄደ የሁለተኛ ደረጃ ደብተርና ካርታ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

3. Makes the pioneer landholders, who have been living in the grand irrigation projects that are developed in modern way, get secondary level certificate and map by legally taking place land re-distribution.

4. ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንበችና መመሪያዎች በዞኑ ውስጥ ለማስፈጸም ያመቸው ዘንድ አግባብ ያላቸውን አካላት ጥረት ያስተባብራል፤ አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

4. Coordinates the effort of pertinent bodies in the zone so as to make conducive to implement this proclamation and regulations and directives to be issued; gives the necessary professional support.

5. በስሩ የሚገኙትን አደረጃጀቶች በየጊዜው ያጠናክራል፣ ለሙያተኞቻቸው ተገቢው ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ተግባራዊ አፈጻጸማቸውን በቅርብ ይከታተላል፡፡

5. Periodically strengthens the organizations under it; makes to be given the appropriate training for their experts, and closely follows their practical implementations.

6. በስሩ በታቀፉ ወረዳዎች ውስጥ የተጠቃለለ የትኛውም የገጠር መሬት ወደ ከተማ ክልል ከመካተቱ በፊት ወይም በሚካተትበት ወይም ለሌላ ለማናቸውም አገልግሎት በሚውልበት ጊዜ አርሶ-አደሮች ላይ መጉላላት እንዳይደርስ ሂደቱንም ሆነ ሽግግሩን እስከ መጨረሻው ድረስ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡

6. Leads and coordinates the process and transition upto the end before or at the time of any rural land embraced under its wereda is encorporated into a town boundary or when it is used for any other service in order not happen a delay on the farmers.

7. የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤቶች በሚሰጧቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ቅር የተሰኙ ወገኖች በይግባኝ የሚያቀርቧቸውን አቤቱታዎች ተቀብሎ ያጣራል፣ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

7. Examine and gives appropriate decision by receiving the appeals submitted by parties who disagreed on the administrative decisions given by wereda rural land administration and use offices;

8. በዞኑ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችም ሆኑ የግል ተቋማት ከገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጋር በተገናኘ ማናቸውንም ተግባራት በሚያከናውኑበት ወይም መሬትን ለተለያዩ ጥቅሞች በሚያውሉበት ጊዜ በዚህ አዋጅ ውስጥ የሰፈሩትን ግዴታዎች አክብረው ስለመፈጸማቸው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

8. Follows and controls the government offices as well as private institutions found in the zone about their implementation respecting the obligations provided in this proclamation at the time of implementing any functions related with the rural land administration and use or using the land for different benefits.

48. የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

48. Power and Function of Wereda Rural Land Administration and Use Office

በወረዳ ደረጃ የተቋቋመ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት በተደራጀበት ወረዳ ውስጥ ይህንን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

The rural land administration and use office established at a wereda lvel, in the wereda where it is organized, has the following particular powers and functions in relation to implementing this proclamation:

1. በወረዳው ውስጥ የሚገኘውን የገጠር መሬት ዓይነትና መጠን አጥንቶና መዝግቦ ይይዛል፤ አስተዳደሩንና አጠቃቀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

1. Keeps by studying and registering the type and amount of rural land found in the wereda; follows and controls the administration and use.

2. መሬቱ በተለያዩ ምክንያቶች ምርታማነቱን እንዳያጣና ከጥቅም ውጭ እንዳይሆን የመሬቱ ተጠቃሚዎች በይዞታቸው ላይ የተለያዩ እንክብካቤዎችን ስለ ማድረጋቸው ይከታተላል፤ መሬታቸውን በአግባቡ ይዘው ለተገኙት ወገኖች የተለያዩ የማትጊያ ዘዴዎችን ይቀይሳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ግዴታቸውን በማይወጡት ላይ ደግሞ ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳል።

2. Follows about different cares the land users make in order not the land lose its productivity due to different reasons; designs and implements different incentive mechanisms for parties found to keep their land properly; and takes appropriate measure on those who do not carryout their obligations.

3. መሬትን በማስተዳደርና አጠቃቀሙን በመወሰን ረገድ በወረዳዉ ዉስጥ ከታቀፉ የቀበሌ አስተዳደር ጽሕፈት ቤቶች በኩል የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ያጠራል፤ አስተዳደራዊ ዉሳኔዎችን ይሰጣል፡፡

4. እንደሁኔታው ባህላዊና ዘመናዊ የቅየሳ ዘዴዎችን በመጠቀም እያንዳንዱን የገጠር መሬት ይዞታና ማሳ ይመዘግባል፤ በምዝገባው መሠረት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ ይሰጣል፡፡

5. በወረዳው ውስጥ የገጠር መሬት ይዞታ መብት የተሰጣቸው ግለሰቦች የይዞታ መብታቸውን እንዳግባብነቱ በውርስ፣ በኪራይ፣ በስጦታ ወይም በለውጥ የሚያስተላልፉበትን ስርዓት ይዘረጋል፤ በመሬት ይዞታ ላይ የሚካሄዱ ለውጦችን በየጊዜው እየመዘገበ መረጃውን ወቅታዊ ያደርጋል፡፡

6. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ለገጠር ቀበሌ ማዕከላትና አዳዲስ ለሚፈጠሩ አነስተኛ ከተሞች የመሬት አጠቃቀም ፕላን ወይም ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ተበታትኖ የሚኖረውን አርሶ-አደርና ከፊል አርብቶ-አደር ወደ አንድ ማዕከል በማሰባሰብ ሁለንተናዊ እድገት ለማምጣት የሚያግዙ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

7. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለሕዝብ ጥቅም ታልሞ በሚወሰድ እርምጃ ምክንያት ከመሬታቸው የሚፈናቀሉ ባለ ይዞታዎች በቅድሚያ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፈላቸውና አማራጭ የኑሮ መሠረት እንዲያገኙ ሁኔተዎችን ያመቻቻል፡፡

3. Examines, gives administrative decision_regarding grievances on land administration and land use submitted through kebele administration offices embraced in the wereda.

4. Registers every landholding and plot as the case may be by using traditional and modern surveying methods and gives a landholding certificate based on the registration.

5. Designes a system that individuals who are given the right of rural landholding in the wereda to transfer their holding rights as the case may be through sucession, rent, donation or exchange. Updates by periodically registering changes takenplace on land.

6. Prepares land use plan for the rural kebele centers and newly created small towns in colaboration with pertinent bodies; carries out functions those bring all-rounded development by collecting the dispersed farmers and semi-pastoralists to one center.

7. Facilitates conditions that displaced landholders_for public purpose, to be paid commensurate compensation and get an alternative living base in collaboration with concerned bodies.

8. በዘመናዊ መንገድ በሚለሙ ትላልቅ የመስኖ-ልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ የሚኖሩ ቀደምት ባለይዞታዎች በሕግ አግባብ የመሬት ሽግሽግ እየተካሄደ የሁለተኛ ደረጃ ደብተርና ካርታ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

9. በከተማ አስተዳደር ክልል የተጠቃለሉ የገጠር መሬት ባለይዞታዎች መሬት-ነክ በሆኑ የአስተዳደርና የአጠቃቀም ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤ ይመዘግባል፤ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተርና ካርታ ይሰጣል፡፡

10. በቀበሌና በንዑስ ቀበሌ ደረጃ የተቋቋሙ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎችንና በዚሁ ደረጃ የተመደቡ ባለሙያዎችን ይደግፋል፤ የመሬት አስተዳደሩ እና አጠቃቀሙ ተግባር አዋጁ በሚጠይቀው መሠረት እየተከናወነ ስለ መሆኑ በቅርብ ይከታተላል፣

11. ለተግባሩ የተመረጡ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አባላት ተገቢውን ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

12. በወረዳው ውስጥ የመሬት አስተዳደርንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፡፡

49. የቀበሌ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

በቀበሌ ደረጃ የተቋቋመ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽህፈት ቤት ይህንን አዋጅ በቀበሌው ውስጥ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

8. Makes the pioneer landholders, who have been residing in the grand irrigation projects developed in modern way, get secondary level certificate and map by legally taking place land re-distribution.

9. Decides on the rural landholders that are embraced under boundary of the city administration concerning land-related administration and use cases, registers and gives a holding certificate and map.

10. Supports the rural land administration and use committees that are established at kebele level and assigned experts thereby; closely follows up the implementation of the rural land administration and use function whether it is in accordance with the proclamation or not.

11. Makes the rural land administration and use committee members, those are selected for the function, get the appropriate training.

12. Keeps and protects data concerning the land administration and use in the wereda.

49. Power and Function of Kebele Rural Land Administration and Use Office

The rural land administration and use office established at a kebele level has the following particular powers and functions in implementing of this proclamation in a kebele:

1. በቀበሌው ውስጥ የሚገኘውን የገጠር መሬት ዓይነትና መጠን አጥንቶና መዝግቦ ይይዛል፤ አስተዳደሩንና አጠቃቀሙን በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
2. መሬቱ በተለያዩ ምክንያቶች ምርታማነቱን እንዳያጣና ከጥቅም ውጭ እንዳይሆን የመሬት ተጠቃሚዎች በይዞታቸው ላይ የተለያዩ እንክብካቤዎችን ሰለ ማድረጋቸው ይከታተላል፤ መሬታቸውን በአግባቡ ይዘው ለተገኙት ወገኖች የተለያዩ የማትጊያ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ግዴታቸውን በማይወጡት ላይ ደግሞ ተገቢ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ በሌሎች ሥልጣኑ ባላቸዉ አካላት እንዲወስድባቸው ያደርጋል፡፡
3. በቀበሌው ውስጥ የገጠር መሬት ይዞታ የተሰጣቸው ሰዎች የይዞታ መብታቸውን እንዳግባብነቱ በውርስ፣ በኪራይ፣ በስጦታ ወይም በለውጥ ለማስተላለፍ የሚያቀርቡለትን ጥያቄ ተቀብሎ ለዚሁ በተዘረጋው ስርዓት መሠረት ያስተናግዳል፡፡
4. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በስሩ ለታቀፉት የገጠር ማዕከላት የመሬት አጠቃቀም እቅዶችን በማዘጋጀት ይሳተፋል፤ የማዕከላቱን ተጠቃሚዎች ይለያል፡፡
5. በቀበሌ ደረጃ የተዘጋጀውን የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለተጠቃሚዎች ያስረክባል፣ ዕቅዱን የተረከቡት ባለ ይዞታዎች ግዴታቸውን ባልተወጡ ጊዜ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንዲወሰዱ ያደርጋል፡፡

1. Keeps by studying and registering the type and amount of the rural land in the kebele; closely follows and controls the administration and its use.
2. Follows about different cares the land users make in order not the land to lose its productivity and be out of use due to different reasons; designs and implements different incentive mechanisms for parties found to keep their land properly; and takes appropriate measure on those who do not carryout their obligations as well as causes to be taken by the other authorized bodies.
3. Treats individuals who are given the right of rural landholding in the kebele to transfer their rights as the case may be through succession, rent, and donation or exchange accordingly the system designed for this when they present requests.
4. In collaboration with concerned bodies, participates in preparing land use plans for rural centers embraced under it; identifies beneficiaries of the center.
5. Submits the land use plan prepared at the kebele level to the users; takes measures when those who received the plan do not carryout their obligations; causes to be taken.

6. ለሕዝብ ጥቅም ታልሞ በሚወሰድ እርምጃ ምክንያት ከገጠር መሬታቸው የሚፈናቀሉ ባለይዞታዎች በቅድሚያ ተመጣጣኝ ካሳ እንዲከፈላቸውና አማራጭ የኑሮ መሠረት እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል፡፡

6. Works with concerned bodies commensurate compensation to be paid and get an alternative livelihood for displaced landholders for public purpose.

7. በዘመናዊ መንገድ በሚለሙ ትላልቅ የመስኖ-ልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ የሚኖሩ ቀደምት ባለይዞታዎች በሕግ አግባብ የመሬት ሽግሽግ እየተካሄደ የሁለተኛ ደረጃ ደብተርና ካርታ ያገኙ ዘንድ በሚደረገው እንቅስቃሴ ይተባበራል፡፡

7. Collaborates the pioneer landholders, who have been residing in grand irrigation projects developed in modern way, to get secondary level certificate and map by legally taking place land re-distribution.

8. በቀበሌና በንዑስ ቀበሌ ደረጃ የተቋቋሙትን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች የሥራ እንቅስቃሴ በቅርብ ይከታተላል፤ አሠራራቸውን በሕብረተሰቡ ያስተቻል፤ ያስገመግማል፡፡

8. Closely follows the implementation of rural land administration and use committee those are established at kebele level and sub-kebele levels; makes their work to be criticized and evaluated by the society.

9. የመሬት አስተዳደርንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፣ ይጠብቃል፡፡

9. Appropriately keeps and protects data concerning land administration and use.

50. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

50. Function and Responsibility of Rural Land Administration and Use Committee

1. በቀበሌ ደረጃ የተቋቋመ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ከወረዳው ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት ባለሙያ ጋር በመተባበር ይህንን አዋጅ በቀበሌው ውስጥ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. The rural land administration and use committee established at a kebele level, in collaboration with the wereda rural land administration and use office expert, has the following particular function and responsibilities in implementing this proclamation:

ሀ. በቀበሌው ውስጥ የሚገኘውን የገጠር መሬት ያስተዳድራል፤

ለ. ከነዋሪው ሕዝብ በኩል የሚቀርቡለትን የመሬት ጥያቄ እየተቀበለ በማጣራትና ቅደም ተከተል በማስያዝ ለተጠቃሚዎች ፍትሀዊ ድልድል እንዲካሄድ ያደርጋል፤

ሐ. ከወረዳው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽሕፈት ቤት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በቀበሌው ውስጥ የሚገኙትን የመሬት ባለይዞታዎችና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸውን ሌሎች ሰዎች ዝርዝር መዝግቦ ይይዛል፤

መ. ማናቸውም የገጠር መሬት ድልድል፣ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር አሰጣጥ፣ አንድን ቦታ ለገጠር ቀበሌ ማዕከል ምሥረታ የማዋል ወይም የወል መሬትን ለግል መጠቀሚያ የማከፋፈልና የአንድን መሬት አገልግሎት የመለወጥ ተግባር እንዲሁም ለሕዝብ አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር የመሬት ይዞታን ወይም የመጠቀም መብትን የሚያግድ ወይም የሚያሳጣ ማናቸውም ውሳኔ በቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ተሳትፎ የተደገፈ መሆኑን ያረጋግጣል።

A. Administers the rural land found in the kebele;

B. Makes fair distribution for users to be carriedout by receving, checking and ordering, the land request from the resident population;

C. Keeps registering the landholders and other persons list who are given the holding certificate found in the kebele based on the directive given by the wereda rural land administration and use office.

D. Assures that any rural land distribution, provision of holding certificate, using a place for rural kebele center establishement or dividing a communal land for private use and the function of changing the service of a place as well as any decision that blocks the landholder or using right except it is for public benefit is supported by the kebele resident population.

2. የንዑስ ቀበሌ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴዎች ተግባርና ኃላፊነት በደንብ ይወሰናል፡፡

51. የተለያዩ መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የግል ተቋማት ከገጠር መሬት አጠቃቀምና አጠባበቅ ጋር ግንኙነት ያለውን ማናቸውንም ተግባር በሚያከናውኑበት ወይም መሬትን ለተለያዩ ተግባራት በሚያውሉበት ጊዜ በዚህ አዋጅ ውስጥ የሰፈሩትን ግዴታዎች የመፈጸም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

2. በየእርከኑ የተደራጁ የአስተዳደር ምክር ቤቶች የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉባቸው፡-

ሀ. ድንበሮች በግልጽ እንዲካለሉ በማድረግ የአዋጁን ተፈጻሚነት የመደገፍና፣

ለ. ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ተቋማት ጥረት እያስተባበሩ በገጠር ቀበሌ ማዕከላትም ሆነ ከእነዚሁ ማዕከላት ውጪ የሚካሄዱ ሕገ-ወጥ ግንባታዎችን የማስቆም፡፡

2. The function and responsibility of the sub-kebele land administration and use committees shall be determined by law.

51. Functions and Responsibilities of different Government Public Organs

1. The government public organs and private institutions found in the region have the responsibility to implement the obligations provided in this proclamamtion when they perform any function related to the rural land administration and use or when they use land for different functions.

2. The administrative councils organized at every level have the following responsibilities:

A. Supporting the implementation of the proclamation in making boundaries to be demarked clearly; and

B. Stoping illegal buildings takenplace in the rural kebele centers as well as out side these _coordinating with concerned institutions.

ክፍል ስምንት
በገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ላይ የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን

52. በገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ላይ ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ስለሚነሱ ክርክሮች

1. የገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብትን በሚመለከት የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና የሚነሱ ክርክሮች በመጀመሪያ ደረጃ፡-

ሀ. በራሳቸው በባለጉዳዮቹ መካከል በሚካሄድ ውይይትና በሚደረግ ስምምነት እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡

ለ. ተከራካሪ ወገኖች በስምምነት ሊፈቷቸው ካልቻሉ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አስታራቂነት ጉዳያቸው እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር በተደነገገው መሠረት አለመግባባቱ ያልተፈታ እንደሆነ ይኸው ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ጉዳዩ ለአቅራቢያው ወረዳ ፍ/ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡

3. የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ ውሳኔ የሰጠበት ማናቸውም ጉዳይ በ30 ቀናት ውስጥ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል፡፡

4. ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ ከአጸናው ውሳኔው የመጨረሻ ይሆናል፡፡

PART EIGHT
DETERMINING DISPUTES ARISED ON RURAL LANDHOLDING AND USE RIGHT

52. Disputes Created and Debates Arised on Rural Landholding and Use Right

1. Disputes created and debates arised on the rural landholding and use right, at the first phase:

A. It is to be solved through discussion and agreement made by the parties themselves.

B. It is to be their case gets a solution by arbitrators eleceted by them if the debating parties could not resolve in agreement.

2. The case will be submitted to the nearby wereda court within 30 days if the dispute is not resolved in accordance with the provision under sub-article (1) of this Article.

3. An appeal will be submitted to a high court within 30 days on any case that has got decision seen by a wereda court for the first phase.

4. The decision becomes the final if the high court received the appeal confirms the decision made by the wereda court.

5. ይግባኙ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ የሻረው ወይም ያሸሻለዉ እንደሆነ ግን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጨማሪ ይግባኝ ሊቀርብበት ይችላል። ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፣

5. A second appeal may be lodged to the Regional Supreme Court if the high court varies or ammends the decision of the lower court. The decision given by the Supreme Court shall be final.

6. የገጠር መሬትን ከመለካት፣ ከማስተዳደርና ከሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ጋር በተየያዘ የወረዳ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤቶች በሚሰጡት አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ይኸው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ክሱን ለወረዳዉ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል። የወረዳዉ ፍ/ቤት የጽ/ቤቱን ውሳኔ ያጸናው እንደሆነ ይግባኙን ለከፍተኛ ፍ/ቤት ሊያቀርብ ይችላል። ይግባኙ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ያጸናው እንደሆነ ውሳኔው የመጨረሻ ይሆናል።

6. Any party disagreed with the administrative decision given by wereda rural land administration and use offices in relation to measuring rural land, administering and other related issues may file suit to the wereda court within 30 days since he has got the decision. He may submit the appeal to a high court if the wereda court confirms the decision of the office. If the high court that received the appeal confirms the decision given by the bottom court, the decision shall become final.

7. በመጨረሻ ደረጃ በተሰጡ የከፍተኛም ሆነ የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን አቤቱታዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊያቀርብ ይችላል።

7. If there is any party who feels fundamental error of law is committed in the decisions given by the final level of the high as well as the Supreme Court, may submit his appeal to the cassasion bench of the Regional Supreme Court.

8. በገጠር መሬት ይዞታና የመጠቀም መብቶች ረገድ የሚነሱ ክርክሮች ከመደበኛ ፍርድ ቤት እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ደግሞ አግባብ ካለቸው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋማት ዉጭ በሌላ በማናቸውም አካል ሊታዩ አይችሉም፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

8. Debates arising on rural land holding and use right may not be seen other than regular court and the pertinent rural land administrative and use institutions from administrative issues. Details will be determined by a regulation.

53. በውክልና ስለመከራከር

በክልሉ ፍትህ ቢሮ ስር የታቀፉትን የደረጃውን አቃቢያነ-ሕግ ጨምሮ ለዚሁ ሕዝባዊ አገልግሎት በሕግ እውቅና የተሰጠው የትኛውም አካል በገጠር መሬት የመጠቀም መብታቸውን ለማስከበር የመከራከር አቅም የሌላቸውን ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ አቅመ ደካሞች፣ ሴቶችና አረጋውያንን ወክሎ በመደበኛ ፍርድ ቤቶችም ሆነ አግባብ ባላቸው የአስተዳደር ተቋማት ፊት ሊከራከርላቸዉ ይችላል።

53. Litigating through Representative

Including prosecutors embraced under the regional justice bureau in every level, anybody who is legally recognized to render this public service may debate representing children who lost their parents, disables, weaklings, women and ageds before regular courts as well as pertinent administrative institutions in order to protect the right of using their rural land.

ክፍል ዘጠኝ

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

54. የፍትሐብሔር ሕግ አግባብነት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15፣ 16 እና 17 ያልተሸፈኑ የገጠር መሬት ኪራይ፣ ስጦታ፣ ውርስና ሌሎች ፍትሀብሔር ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ እንደነገሩ ሁኔታ አግባብነት ያላቸዉ የ1952 ዓ.ም የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

PART NINE

MISCELANEOUS PROVISIONS

54. Relevance of Civil Law

The relevant provisions of the 1960 civil code shall apply, as the cases may be, regarding rent of the rural land, donation, inheritance and other matters related to civil issues which are not covered under Articles 15, 16 and 17 of this proclamation.

55. ስለ ይርጋ

የገጠር መሬትን በወረራ ወይም በሌላ በማናቸውም ሕገ-ወጥ መንገድ ይዞ በመገልገል ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሰው መሬቱን እንዲለቅ በማንኛውም ሌላ ሰው ወይም ሥልጣን ባለው የመንግሥት አስተዳደር አካል ሲጠየቅ ወይም በመደበኛ ፍርድ ቤት ሲከሰስ የይርጋ ጊዜ ገደብን በሥነ-ስርዓት መቃወሚያነት ሊያነሣ አይችልም።

55. Period of Limitation

Any person found to be using rural landholding in invasion or in any illegal means can not raise the period of limitation as objection when he is asked by any other person or authourized government body or accused before court.

56. የፍርድ ቤት ውሳኔ በገጠር መሬት ይዞታ ላይ ስለሚኖረው ሕጋዊ ውጤት

ማንኛውም የገጠር መሬት ባለ ይዞታ የፍርድ ቤት ውሳኔን ለማስፈጸም በሚሰጥ ትዕዛዝ ከይዞታው አይፈናቀልም ወይም ይዞታው ለዕዳ መክፈያ በሚል ለሌላ አካል ሊተላለፍ አይችልም።

56. Legal Effect of Court Decision on Rural Land

Any rural landholder is not displaced from his holding or his holding is not transferred to other party for debt payment by order of implementing court decision.

57. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ከገጠር መሬት ይዞታና አጠቃቀም ጋር በተያያዙ በሌሎች ሕጐች የተቋቋሙ መብቶችና ግዴታዎች ቀደም ሲል የነበሩ ሕጐችን መሠረት አድርገው እስከተገኙና ይህንን አዋጅ በግልጽ እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ፍርድ ቤት ቀርበው በመታየት ላይ ያሉ ማናቸውም መሬት-ነክ ጉዳዮች በተጀመሩበት አግባብ የመጨረሻ እልባት እንዲያገኙ ይደረጋል።

57. Transitory Provisions

1. The application of rights and obligations established_ related to rural land holding and use before the effective date of this proclamation become applicable as far as they are found in line with previous laws and do not clearly contradict with this proclamation.
2. Any land-related cases those have been evaluated in court before the issuance of this proclamation shall get solution pursuant to their commencement.

58. የመተባበር ግዴታና የወንጀል ኃላፊነት

1. ማንኛውም ሰው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የጣሰ ወይም አፈጻጸማቸውን ሆነ ብሎ ያሰናከለ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ በተደነገገው መሠረት ይቀጣል።

58. Obligation of Collaboration and Criminal Responsibility

1. Any person has an obligation to collaborate with pertinent bodies to implement this proclamation.
2. Any person who violates the provisions of this proclamation or deliberately hampers their implementation is punished by an appropriate criminal law.

59. ስለተሻሩና ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸዉ ሕጎች

1. የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 148/1999 ዓ.ም እንደተሻሻለ ተሸሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል።

2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

60. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

2. ቢሮው ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

59. Repealed and Inapplicable Laws

1. The Revised Amhara National Regional State Rural Land Administration and Use Determination Proclamation No 133/2006 as amended by Proclamation No 148/2007 is repealed and replaced hereby this proclamation.

2. Any law, regulation, directive or customary practice shall not have application on matters covered by this proclamation.

60. Power to Issue Regulation and Directive

1. The council of regional government may issue regulations necessary to implement this proclamation.

2. The bureau may issue directives to implement this proclamation and regulations to be issued based on the proclamation.

61. በሥራ ላይ ስለሚቆዩ የማስፈጸሚያ ደንቦችና መመሪያዎች

ተሻሽሎ በወጣዉና እስካሁን ጸንቶ ሲሰራበት በቆየዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 ዓ.ም አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ (1) (እንደተሸሻለ) መሠረት የወጣዉ የዚሁ አዋጅ ማስፈጸሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 51/1999 ዓ.ም እና እርሱን ተከትለዉ የወጡት ልዩ ልዩ መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር በግልጽ እስካልተቀረኑ ድረስ በኣዳዲስ የማስፈጸሚያ ሕግጋት እስኪተኩ ተፈጻሚነታቸዉ ይቀጥላል።

61. Applicable Implementation Regulations and Directives

The Council of the Amhara National Regional Government Regulation No 51/2007, which is issued based on the revised rural land administration and use determination proclamation number 133/2006 Article 33 sub-article (1) (as amended) for the implementation of this proclamation, and different directives issued following this _their application continues as far as they do not clearly contradict with this proclamation and until they are replaced by new implementing laws.

62. አዋጁ ስለሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባሕርዳር

ጥቅምት 20 ቀን 2010 ዓ.ም

ገዱ አንዳርጋቸው

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዝዳንት

62. Effective Date

This proclamation shall come to force as of its publication in the Zikre-Hig Gazatte of the regional state.

Done at Bahir Dar

This 30th Day of October, 2017.

Gedu Andargachew

President of the Amhara National Region.